## ምዕራፍ ሦስት

# ሐሰተኞች ነቢያትና አስተማሪዎች በእግዚአብሔር ቃል

ክርስቲያን እንደመሆናችን የምናነብበውና የሚመራን መጽሐፍ አለን። እውነትን ከስሕተት አንጥረን እንድናይ የሚረዳን ቅዱስ ቃሉ ነው። ከዚህ ቅዱስ ቃል ጋር በብዙው ልንተዋወቅ ያሻናል። በክርስትና ሕይወት ላለመብሰል ከትልልቆቹ ምክንያቶች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚገባ ያለማወቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለማወቅ የግድ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት የለብንም። አጋጣሚው ከተገኘ ግን ይህ ማምለጥ የሌለበት ዕድል ነው። ይህም ባይሆን በአምላካችን ፊት በቅንነት ሆነን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቃሉን ስናነብ እውነቱን እንረዳለን። ጠንቅቀን የማንረዳቸው ክፍሎች ቢኖሩም መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዶች እንደሚገምቱት የምስጢሮች ስብስብ አይደለም። በአንጻሩ ደግሞ ግልጽ የሆነው እያንዳንዱ ሐረግና ዐረፍተ ነገር የግድ መተርጎም የለበትም። እንዲህ ሲያደርጉ አንዳንዶች ውሉ እስኪጠፋ ያወሳስቡታል። ምዕራፍ አራት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ለሚያጠኑና ለሚሰብኩ ለጠቅላላ አቀራረብና ግንዛቤ የሚሆን መጠነኛ እርዳታ ይዞአል።

የሐሰት አስተማሪዎች በገነኑበት ሥፍራ ሁሉ ከታዳሚዎቻቸው የሚያገኙት አራት ዓይነት ምላሾች አሉ። የመጀመሪያው፥ “ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲህ ያደርጉላቸው ነበርና” እንደተባሉት ስለ እነርሱ መልካምን መናገር ነው። ሁለተኛው ምላሽ፥ ‘ምን አገባኝ፥ የራሳቸው ጉዳይ፥ እኔና ነፍሴ ደህና’ የሚል ነው። ሦስተኛው፥ ተቃውሞ አውግዞና ገዝቶ ማባረርና ማሳደድ ነው። አራተኛው፥ በቅንነት ለማረምና ለመመለስ፥ ካልሆነም ስሕተቱን ለመግለጥና ለማስጠንቀቅ መጣር ነው። ትክክለኛ ነው የምለው ይህንን በመጨረሻው ነጥብ የተጠቀሰውን ነው። ስሕተትን በጭፍን መቃወም ብቻ ሳይሆን መግለጥና ከእውነቱ ጋር አነጻጽሮ ማሳየት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በተጨባጭ ማስረጃ መደገፍ





ያስፈልጋል። ያም ማስረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ብቁ፥ ተጨባጭና በቂ ማስረጃ ከቶም አይኖርም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐሰተኞች ነቢያትና አስተማሪዎች በብዙ ስፍራዎች በግልጽ ይናገራል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተሰጡትን አጫጭር ማብራሪያዎች ብቻ ከማንበብ በፊት በተቻለ መጠን የመነሻ ጥቅሶቹን በዐውዳቸው እንዳሉ በጥሞና ብታነብቡ ይበልጥ ልትማሩባቸው እንደምትችሉ አምናለሁ። ስለ ዐውድ ወይም ዐውደ ምንባብ በስነ ትርጓሜ ክፍል በመጠነኛ ስፋት ተጽፎአል። ለመግቢያና ለመግባቢያ ግን ዐውደ ምንባብ ሰፋ ያለ ክፍለ ምንባብ ነው። ይህም ከአንድ የሚጠና ክፍል ፊትና ኋላ ያሉ ጥቂት ወይም ብዙ የተያያዙ ክፍሎችን ይይዛል።

## ዘዳግም 13፥1-5

*በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሳ፥ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ፥ እንደነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም፥ እርሱም፥ ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል እና ምልካቸውም ቢልህ፥ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወድዱት እንደሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ። አምላካችሁን እግዚአብሔርን ተከተሉ፥ እርሱንም ፍሩ፥ ትእዛዙንም ጠብቁ፥ ቃሉንም ስሙ፥ እርሱንም አምልኩ፥ ከእርሱም ጋር ተጣበቁ። አምላክህ እግዚአብሔር ትሄድባት ዘንድ ካዘዘህ መንገድ ሊያወጣህ፥ ከግብጽ ምድር ካወጣችሁ ከባርነትም ቤት ካዳናችሁ ከአምላካችሁ ከእግዚአብሔር ሊያስታችሁ ተናግሮአልና ያ ነቢይ ወይም ያ ሕልም አላሚ ይገደል፥ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ አርቅ።*

እስራኤል ሐሰተኞች ነቢያትን ከሚያውቁበት ሁለት ዋና ዋና መንገዶች አንደኛው ነቢያቱ በእግዚአብሔር ስም መናገርና ያለመናገራቸው እና ሁለተኛው የተናገሩት ነገር መፈጸሙና ያለመፈጸሙ ናቸው። እኒህን ሁለት ነገሮችና ይህንም ስለሚያረጋግጡበት የተጻፈ መፈተኛ በዘዳ. 18፥20-22 እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን፥

*ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል። በልብህም እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፥ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፥ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።*

ከዚህ ክፍል የምንረዳው በብሉይ ኪዳን እውነተኛ ነቢያት የሚናገሩት በእግዚአብሔር ስም መሆኑንና የሚናገሩት ነገርም በእርግጥ ተፈጻሚ እንደሚሆን ነው። በአንጻሩ ደግሞ ሐሰተኞች ነቢያት የሚታወቁት በእግዚአሔር ስም ቢናገሩም እንኳ የተና ገሩአቸው ነገሮች ተፈጻሚ ባለመሆናቸው ነው። በተጨማሪ ኤር.

28፥7-9 ተመልከቱ። በእግዚአብሔርም ስም ተናግረው፥ ነገሮቹም ተፈጽመው፥ እነርሱ ሐሰተኞችስ ከሆኑ? ዘዳግም 13 ይህንም ይነግረናል።

በዘዳግም 13 የተጻፈው በመጠኑ ጠለቅ ያለ ነው። በዚህ ክፍል ሁለት ምንጮች ይታያሉ። በቁጥር 3 ላይ ራሱ እግዚአብሔር ሊፈትናቸው ይህን እንዳደረገ ይናገራል። ይህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ዘንድ የሚያደርገው ገንቢና አዎንታዊ ፈተና ነው። እግዚአብሔር በክፉ ሳይሆን ለበጎ ውጤት ይፈትናል። አብርሃምና ኢዮብ ተፈትነው ያለፉ የአማኞች ምሳሌዎች ናቸው። በዚህ ክፍል የምናገኘው ሁለተኛው የፈተና ምንጭ ደግሞ ነቢዩ ነው። ይህ ሕልም አላሚ ወይም ነቢይ የሚናገርበት ሁኔታ ተራና ግምታዊ ብቻ አይደለም። 'ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ፥ እንደነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም' ይላልና ሰውየው ምልክት መስጠት ብቻ ሳይሆን ምልክቱም ሊፈጸም የሚችልበት ሁኔታም ነው የተገለጠው። እንግዲህ ምልክትና ተአምራት መስጠትና የምልክቶቹና የተአምራቱ መፈጸም ብቻም የእውነተኛ ነቢይ መለኪያ ላይሆኑ ነው ማለት ነው። ዘዳግም 13 ለነቢዩ እውነተኛነትና ሐሰተኛነት ሌላ የመመዘኛ ማሰሪያም አድርጎለታል። ያም እራሱንና ሌላውንም ከእግዚአብሔር ጋር ማጣበቁና እግዚአብሔርን በማምለክ መጽናቱ ነው። ትንቢቱን ከተናገረ በኋላና ትንቢቱም ከተፈጸመ በኋላ፥ ሄደን ሌሎችን አማልክት እና ምልክ፥ እንከተል ቢል ያ ሰው የሳተና የሚያስትም ነው። ምልክት ታይቶአል፥ ተአምርም ተሠርቶአል፥ ውጤቱ ግን ወደ ሌላ ማመልከትና መጋበዝ ሆነ። ሙሴ ትልቅ ማስጠንቀቂያ ነው ለእስራኤል የሰጣቸው።

የሚስብ ነገር ያላቸው መሪዎች፥ የተናገሩት የተፈጸመላቸውና ምልክትና ተአምራት ያሳዩ ነቢያት ሁሉ ሁሌም ከእግዚአብሔር የተላኩ ናቸው ማለት አይደለም። ሞቅ ብሎአቸው ሞቅ የሚያደርጉ፥ ጮኸው የሚያስጮኹ፥ የሰዎችን ስሜት ከማይደረስበት ላይ አውጥተው የሚሰቅሉ አንዳንድ አገልጋዮች በዚህ የጋለ ስሜታዊ መሳከር ውስጥ እንግዳ ነገሮችን ሊናገሩ ይችላሉ። እነዚህ እንግዳ ነገሮች መጥፎ ላይሆኑ ወይም ጥሩ ሊመስሉን ይችላሉ። ቁም ነገሩ ግን መጥፎ ያለመሆናቸው ወይም ለኛ ጥሩ መምሰላቸው ሳይሆን የሥልጣናችን ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማሉ ወይም አይስማሙም የሚለው መሆን አለበት።

ዛሬ ሰዎች፥ '. . . ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር' እያሉ በእግዚአብሔር ስም ትንቢት ወይም ሌላ ነገር ሲናገሩ በቅንነትና በቅዱስ ቃሉ መመርመር ይገባናል። መመርመሩ ከእኛ እጅግ የራቀ ሊመስለን ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ምትሃታዊ ነገር አይደለም። በውስጣችን ያደረው መንፈስ ቅዱስ ምስክርነቱን እውነት መሆንና





ያለመሆኑን ሊያሳየን ወይም ቃሉን አጉልቶ ሊያስታውሰን ይችላል። ከዚያም ወዲህ ደግሞ በጤናማ አእምሮ እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን መጠየቅ እትክክለኛ ድምዳሜ ላይ ሊያደርሰን ይችላል። በማያሳስት ሁኔታ ግን የነገሮችን እውነትነትና ሐሰትነት ለመገንዘብ ቃሉን መመርመር አማራጭ የሌለው ጤናማ መንገድ ነው።

ትምህርታቸው ወይም ትንቢታቸውና ተግባራቸው፥ ራሳቸውን ወይስ ክርስቶስን ያጎላል? ፍቅርን ያራምዳል ወይስ ጥላቻንና መከፋፈልን ይዘራል? ያነጣጠሩት በእግዚአብሔር ክብር ላይ ነው ወይስ በራሳቸው ወይም በሌላ? የተናገሩት ነገር ከዚህ በፊት ካወቅነውና ከቃሉ ከተረዳነው እውነት የራቀ ነው ወይስ አይደለም? የሚናገሩት ነገር ለአእምሮአችንና ለነፍሳችንም ጭምር ነው ወይስ ለስሜታችን ብቻ? ለስሜታችን ደስ ባይለውም መራራ የሚመስለውን እውነትና ኃጢአት ይጠቁሙናል? ወደፊታዊ ትንቢት ከሆነ ከዚህ በፊት የተናገሩት ነገር በትክክል ተፈጽሞ ያውቃል? ወይስ ያለመፈጸሙን ሲያዩ ከልሰው፥ አርመው አሻሽለው ያቀርቡታል? የሚናገሩት ነገር በቃሉ ከተገለጡት የእግዚአብሔር ባህርያት ጋር ይጣጣማሉ ወይስ ይጋጫሉ?

እውነትን ተናግረው እግዚአብሔርን የሚያሳዩን አገልጋዮች እንዳሉ ሁሉ፥ እውነትም ሊሆን ይችላል ግን ስሜታችንን የሚያነሳሳ ነገር ተናግረው ወደ ራሳቸውን የሚስቡን ሰዎችም አሉ። እውነተኛ ነገር እየተናገሩ ሰዎችን በስሕተት ተግባር ወይም መንገድ መምራት ከባድ ነገር አይደለም። እግዚአብሔር በደፈናው አዳዲስ ነገሮችን ሁሉ የሚጠላ አምላክ ሳይሆን እንደ በሙሴ በኩል እንደተነገረን ማስጠንቀቂያ ነገሮችን፥ በተለይም መንፈሳዊ ምንጭ ያላቸውን ነገሮች እንድንመረምር ይፈልጋል። 1ዮሐ. 4፥1 የሚነግረንም ይህንኑ ነው።

በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ሰዎችም የሚሰሙአቸውን ነገሮች በቃሉ እየፈተኑ ከቃሉ ጋር የተስማሙትን በመቀበል የማይስማሙትን ደግሞ በሁለት እግሮች ቆመው በሁለት እጆች መጋፋት መቻል አለባቸው። በዘዳ. 13፥6-7 ላይ ይህ አሳችነት ከምልክትና ተአምራት ብቻ ሳይሆን ከዝምድና ወይም ከቅርብነትም ጋር ሊያያዝ እንደሚችል እናስተውላለን። ሐሰተኛ ነቢያት የተጣመመ ትምህርታቸውን የሚያራግፉባቸውንና መጀመሪያ የሚያገኙአቸውን ተከታዮች የሚቀዱባቸው ምንጮች ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጆች፥ በቀላሉ የሚያምኑና ፍርሃት ያለባቸው አማኞች፥ በጥቅም የሚደለሉ ወይም በሽንገላና በሐሰተኛ ትንቢቶቻቸው የሚታለሉ ሰዎች ናቸው።

## 1ነገ. 18 እና 19 እንዲሁም 2ዜና. 18፥4-11

ጥንትም ሆነ በዘመናችን መሪዎችና ነገሥታት ለእነርሱ የሚመቹ ትንቢተኞችን በዙሪያቸው ይሰበስባሉ። ለነገሩ ነገሥታትና መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰዎችም ሁሉ ለጆሮአቸው የሚጥም ነገርን የሚናገሩአቸውን ይፈልጋሉ። በመጨረሻው ዘመንም ለራሳቸው አስተማሪዎችን እንደሚያከማቹ የተነገረላቸው እንዲህ ያሉቱ ና ቸው። እንዲህ ያሉቱ ትንቢተኞች የእግዚአብሔር ነቢያት ሳይሆኑ የሰው ትንቢተኞች ናቸው። እውነትን መናገርን የማያውቁና የማይወዱ፥ ሊሞክሩ ቢፈልጉ እንኳ የማይፈቀድላቸው ናቸው። ከላይ በተጠቀሱት ክፍለ ምንባቦች ውስጥ የምናያቸው ሁለት ነቢያት ኤልያስና ሚክያስ ናቸው። የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና ሚስቱ ኤልዛቤል 850 የሚያህሉ የበኣልና የማምለኪያ ዐፀድ ትንቢትኞችን ሰብስበው ይቀልቡና ሐሰተኛ ሃይማኖት ያስፋፉ ነበር። ኤልዛቤል የሲዶና ንጉሥ ልጅ ናት። ሲዶናውያን በኣል የሚባለው አምላክ አምላኪዎች ናቸው። አክዓብ በዚህች ሚስቱ እንደ እንስሳ የተነዳ ሰው ነበር። እነዚህ በመቶዎች የሚቆጠሩ ትንቢተኞች ለንጉሣውያን ቤተ ሰብ የሚመች ነገር እስከተናገሩ ድረስ እነርሱም ይመቻቸዋል። እነርሱን የሚያበሳጭ ደረቅ እውነት ከተናገሩ ግን ጉድ ይፈላባቸዋል።

ሐሰተኞች ነቢያት ከሰው ዘንድ የሚሰነዘር መከራ የማይደርስባቸው ለሰው የሚመች ነገር ስለሚያቀርቡ ነው። ለእውነተኛ ነቢያት ግን መከራ እንደ ምግብ ነው። ለዚህ ነው ኤልያስ በዚህ ጊዜ በስደት በኮራት ፈፋና በሲዶና በአንዲት መበለት ቤት ተሸሽጎ የቆየው። ለዚህ ነው ሴዴቅያስ የተባለው የንጉሥ ትንቢተኛ ቀርቦ ሚክያስን በጥፊ የመታው። ለዚህ ነው ንጉሡም ስለ ሚክያስ፥ 'እስክመለስ ወደ ግዞት ውሰዱት፥ የመከራ እንጀራ አብሉት፥ የመከራም ውኃ አጠጡት' ብሎ አዝዞ ሲመለስ ሊበቀለው አቅዶ ወደ ሰልፍ የሄደው። ሚክያስ እንደተናገረው ግን ንጉሡ አልተመለሰም። እውነትን የሚናገር ነቢይ የእውነት ወገንና ወዳጅ ባልሆኑት ዘንድ አይወደድም። መጥምቁ ዮሐንስ በሄሮድስ አንገቱን የተቀላው ለንጉሡ የማይመችን እውነት ስለተናገረ ነበር። በአይሁድ ታሪክ እንደተጻፈው ኢሳይያስ በምናሴ በመጋዝ የተሰነጠቀው ወቃሹ ሆኖ ስለተገኘ ነው። ሌሎችም ብዙዎች ነቢያት በእውነተኛ አገልግሎታቸው ሳቢያ ብዙ የግፍ ጽዋ እንደጠጡ ይታወቃል።

ኤልዛቤል የቃልቻ ሥራ የሚሠሩላት ተንባዮች ጥቂት አልነበሩምና ብዙ ዋጋ እያወጣች ታስደስታቸው ነበር። እነርሱም በሐሰተኛ ትንቢታቸው ብድር ይመልሳሉ። በኤልያስ የአንድ ቀን ብርቱና ሰማያዊ አገልግሎት ግን ዕድሜአቸውም የሐሰት ሥራቸውም በአንድ ቀን ተቋርጦ ሁሉም ተገደሉ። በስሕተት መንገድ የሚፋንኑ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነተኛ





ሥራ ማየታቸው ወደ መረዳትና ወደ ንስሃ አያመጣቸውም። እንዲያውም በልበ ደንዳናነታቸው ይቀጥላሉ። በ1ነገ. 18 የሚገኘው የበኣልና የዐፀድ ነቢያት ፉክክር የእግዚአብሔርን ማንነት የሚገልጥ ትንግርት ነበር። ተአምራቱን ካዩ በኋላ እዚያ በነበሩት ሕዝብ ውስጥ የተፈጠረው ለውጥ ታላቅ ነበር። በቁጥር 39 ላይ፥ 'ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግንባራቸው ተደፍተው፥ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው፥ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ' ይላል። በተቃራኒው ግን ኤልዛቤል በኤልያስ እጅ እንደተደረገ የሰማችው ምልክትና ለነቢያቷ ደግሞ አምላኳ የሆነው በኣል ሰምቶ አለመመለሱ ለበቀል በኤልያስ ላይ አነሳሳት እንጂ ልብዋን አልገራውም። ዛሬም ይኸው ነገር ጥቂት ባልሆኑ ሁኔታዎች ሲደረግ ይታያል። መልካም መልካም ብቻ ለሚናገሩ አስተማሪና ሰባኪዎች እንዲሁም ትንቢተኞች ዘብ መቆም እየተለመደ ነው። ብዙዎች በ2ጢሞ. 4፥3 እንደተጻፈው ከእውነቱ በመራቅ የሚጥማቸውንና ምኞታቸውን ብቻ የሚናገሩትን ነቢያትና አስተማሪዎች ለራሳቸው ያከማቻሉ።

በ2ዜና. 18፥17 የምናየው ደግሞ አክዓብንና ኢዮሳፍጥን ነው። ተመሳሳዩን ታሪክ በ1ነገ. 22 እናገኛለን። አክዓብ ከላይ የተጠቀሰችው ሴት የኤልዛቤል ባል የነበረ የእስራኤል ንጉሥ ነው። ኢዮሳፍጥ ደግሞ በዚያኑ ጊዜ የይሁዳ ንጉሥ የነበረ ሰው ነው። እስራኤልና ይሁዳ አንድ ሕዝብ ሳሉ እንደ ሁለት አገርና መንግሥት ሆነው እየኖሩ ብዙ ቆይተዋል። የይሁዳ ዋና ከተማ ኢየሩሳሌም ስለነበረችና በዚያ መቅደሱና ካህናቱም ስለነበሩ ይመስላል የይሁዳ ነገሥታት በከፊል ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው ነበሩ። በእስራኤል ግን አንድም እግዚአብሔርን የሚወድና የሚከተል ንጉሥ ኖሮ አያውቅም። እዚህም የምናያቸው ሁለቱ ነገሥታት በዚህ እይታ አንፃር ይለያያሉ። ኢዮሳፍጥ እግዚአብሔርን ሲፈራና ፈቃዱን ሊያውቅ ሲሻ አክዓብ ግን በሚስቱ ነጂነት ከእግዚአብሔር መንገድ ርቆ የሲዶናውያን አምላክ የበኣል ተከታይ ሆኖአል። ምንም በራሱ ነቢያት ቢከበብም ይህንን ክፋቱንና ጥፋቱን ደፍረው የሚናገሩ ነቢያት ግን አልጠፉም።

ጊዜው ሁለቱ ነገሥታትና ሠራዊታቸው ግንባር ፈጥረው ከሶርያ ሠራዊት ጋር ሊዋጉ የተቃረቡበት ዋዜማ ነበር። አክዓብ አራት መቶ የበኣል ነቢያቱን ሰብስቦ ንጉሡ መውጣት ወይም አለመውጣት እንዳለበት ጠየቃቸው። በታሪኩ ተራ ተከትል ከሄድን እነዚህ ነቢያት የቀደሙት አራት መቶው ከሞቱ በኋላ የተሰበሰቡ ሌሎች ነቢያት ናቸው። ሁሉም እንዲወጣና እንዲዋጋ ይነግሩታል። እንደሚያሸንፍም አስረግጠው ይተነብዩለታል። ኢዮሳፍጥ ግን በውስጡ ካለው እግዚአብሔርን የሚፈራ ልቡና የተነሣ ነገሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ለማወቅ ብርቱ መሻት ስላደረበት

ሌላ ነቢይ መኖር አለመኖሩን ጠየቆ አረጋገጠ። በዘመኑ ያገለግል የነበረ ሚክያስ የሚባል የእግዚአብሔር ነቢይ ነበረ።

አክዓብ ስለ ሚክያስ ለኢዮሳፍጥ ሲናገር፥ 'ክፉ እንጂ መልካም ትንቢት አይናገርልኝም አላልኩህም?' ነበር ያለው። አክዓብ የፈለገው እንደገዛ ነቢያቱ የሚጥመውን እንጂ እውነቱን እንዲናገር አልነበረም። (በተጨማሪ ኢሳ. 30፥10-11 እና ኤር. 14፥13-16 ተመልከቱ።) ቀድሞም አክዓብ ለይስሙላ ወይም ኢዮሳፍጥ ግድ ስላለው ጠየቀ እንጂ የጠየቀው የሚነገረውን ለመታዘዝ አልነበረም። የማያደርጉት ከሆነ ጌታን ምክር መጠየቅ ወይም ፈቃዱን ለማወቅ መጣር ረብ የለውም። ይህ ከአክዓብ አንጻር ሲታይ ነው።

ከሚክያስ በኩል ሲታይ ደግሞ ሌላ እውነት እናገኛለን። እውነተኛውን ነገር መናገርና ከጌታ ጋር መቆም ነቢያቱ ሊደርስባቸው ከሚችለው ተግዳሮችና መከራ ይጋርዳቸዋል ማለት አይደለም። ሚክያስ እውነተኛውን ትንቢት በመናገሩ ግዞትና የመከራ እህል ውኃ ተበየነበት። ጌታን መታዘዝና እውነትን መና ገር መከራን ሊያመጣ መቻሉ እውነት ነው። ቢሆንም ጌታ በአድራጎታችን ባለመደሰቱ ምክንያት በእኛ ላይ የሚያመጣውን ቁጣ ከመቀበል ይልቅ የእግዚአብሔር እውነት ሲነገራቸው ከማይደሰቱ ሰዎች እጅ መከራን መቀበል ይሻላል።

## ኤር. 14፥13-16 (በተለይ 14፥14)

እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚወድ ከክፉ ነገር ይጠብቃቸዋል። ከታዘዙት ከመልካምነቱ እንደሚያጠግባቸውና የማይታዘዙና ዓመጸኞች ከሆኑ ደግሞ ከፍቅሩ የተነሣ እንደሚቀጣቸው ቃሉ ብዙ ያስተምራል። በኤርምያስ ዘመንም ሕዝቡ በድሉ በምድሪቱ ላይ ቅጣት ወረደ፤ በድርቅም ተመታች። ቁጥር 7 ይህን ይገልጥልናል። በቁጥር 13 ላይ ኤርምያስ ሐሰተኞች ነቢያት ለሕዝቡ ሰላም እንጂ ሰይፍና ራብ እንደማይሆን ውሸታም ተስፋ እየሰጡአቸው የመሆናቸውን ስሞታ ለእግዚአብሔር ያቀርባል። በቁጥር 14 ላይ እግዚአብሔር መልስ ሲሰጠው እንዲህ ይለዋል፥

> ነቢያቱ ውሸት በስሜ ትንቢት ይናገራሉ፥ አልላክኋቸውም፥ አላዘዝኋቸውም፥ አልተናገርኋቸውም፥ የውሸቱን ራዕይ፥ ምዋርትንም ከንቱንም ነገር የልባቸውንም ሽንገላ ይሰብኩላቸኋል።

እነዚህ ምዋርተኞች የሆኑ የሐሰት ነቢያት እየተናገሩ ያሉት የልባቸውን ሽንገላና ሕዝቡ የሚፈልገውንና ለስሜቱ የሚጥመውን ነገር ነው። ቅጣቱ የሆነባቸውን ምክንያትና በንስሃ ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱበትን መንገድ አላመለከቱአቸውም።





ሰዎች ከእግዚአብሔር አሳብ እጅግ ርቀው ሳለ በሽንገላ ቃላት ሰላም ከተሰበከላቸው በአንድ ጊዜ ሁለት መጥፎ ነገሮች ይፈጸማሉ። የመጀመሪያው ተግሳጽና ሃይ የሚል ባለመኖሩ በመጥፎ ሥራቸውና ልባቸው ይቀጥላሉ። ሁለተኛው ደግሞ ሰላም ስለተባለ ሰላም መስሎአቸው እየተዘናጉ ለቅጣትና ለጥፋት ይዳረጋሉ። ይህም ዘመን ከዚያ የተለየ አይመስልም። የእግዚአብሔር ምክሩ፥ ተግሳጹ፥ ቁጣው፥ ቅጣቱ ተሟጥጦ ያለቀበት ይመስላል። የሚነገሩት ነገሮች ሁሉ ብልጽግና፥ ሙሉ ጤንነት፥ ፍጹም ፈውስ፥ የተሳካ አገልግሎት፥ የተሟላ ኑሮ፥ እንቅፋት የሌለበት ጉዞ፥ በረከት ብቻ ነው። በግል ጥጋብና በረከት፥ በቤተ ሰብ ባለጠግነትና በረከት፥ በአገር ሰላምና በረከት። ያለንበት ዘመን መልክ ሲመረመር ግን የሚናገረው ሌላ ነው። እነዚህ በረከቶች በራሳቸው መልካም ቢሆኑም ከሚነገሩ ነገሮች ጋር የሰዎቹን አኳኋንና እየሆኑ ያሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች ማጤን በእጅጉ ተገቢ ነው።

## ኤር. 23፥9-32 እና ኤር. 28

በዚህ ክፍል እስራኤል ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆኖ ከእግዚአብሔር እንደጠፋ እናያለን። የጠፉትም ከሐሰተኛ ነቢያት የተነሣ ነው። ሐሰተኛ ነቢያት ብዙ ተከታይና ጆሌ አላቸው፥ ምክንያቱም የሚናገሩት ሁሉ የፍርድ ተቃራኒ ነው። ሕዝቡ ስቶ ከአምላኩ ሲርቅ እያዩም እንደሳቱና እንደጠፉ አያስጠነቅቁም፥ እንዲመለሱም አይመክሩም። ኤርምያስ ግን የሕዝቡን ርኩሰትና የሚመጣባቸውንም ፍርድ ይናገር ነበርና ተጠመደ።

በዚህ በኤርምያስ ምዕራፍ ምንባብ ውስጥ ያኔ የነበሩና ዛሬም ሳይለወጡ ያሉ የሐሰተኛ ነቢያት ባህርያትን እናገኛለን።

1፥ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገሩ ይመስላሉ፥ ወይም ይና ገራሉ፥ ነገር ግን እንደ ትእዛዙ አይኖሩም። ቁጥር 11 እና 14 እንዲህ ይላል፥

> ነቢዩና ካህኑም ረክሰዋል፥ በቤቴም ውስጥ ክፋታቸውን አግኝቻለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር. . . በኢየሩሳሌምም ነቢያት ላይ የሚያስደነግጥን ነገር አይቻለሁ፥ ያመነዝራሉ፥ በሐሰትም ይሄዳሉ፥ ማንም ከክፋቱ እንዳይመለስ የክፉ አድራጊዎችን እጅ ያበረታሉ፥ ሁሉም እንደ ሰዶም የሚኖሩባትም እንደ ገሞራ ሆኑብኝ።

2፥ የእግዚአብሔርን ቃል እና የሚሉትን ትንቢት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ስለማይቀበሉ የራሳቸው ልብ የሚላቸውን ለሰዎች እንደሚመች ቀምመውና አጣፍጠው ያቀርባሉ። ቁጥር 16፥ 26 እና 31 እንዲህ ይላል፥

> ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ፥ ከንቱነትን ያስተምሩአችኋል፥ ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የወጣውን

> ራእይ ይናገራሉ. . . የልባቸውንም ሽንገላ በሚናገሩ በነቢያት ልብ ይህ የሚሆነው እስከመቼ ነው? . . . እነሆ፥ ከምላሳቸው ትንቢትን አውጥተው እርሱ ይላል በሚሉ ነቢያት ላይ ነኝ።

3፥ አድማጮቻቸውና ተከታዮቻቸው ስውርና ስልታዊ በሆነ መንገድ በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምጹና እንዳይታዘዙት ያደርጓቸዋል። ራሳቸውም ደፋሮች፥ ራስ ወዳዶችና ተድላ ፈላጊዎች፥ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ለሚያደምጡአቸው ታማኝ መሆንን የሚመርጡ ናቸው። ይህንንም በማድረግ፥

- የክፉ አድራጊዎችን እጅ ያበረታሉ። (፥14)
- ሰዎችን በመጥፎ መንገድ ያስከትሉአቸዋል። (፥17)
- የእግዚአብሔር ስም እንዲረሳ ለማድረግ ይጥራሉ። (፥27)
- ቃሉን ይሰርቃሉ። (፥30)
- በድፍረት ሕዝቡን ያስታሉ። (፥32)

ኤርምያስ የእነዚህን የሐሰት ነቢያት መልእክትና እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ሲያወዳድር በገለባና ስንዴ ዘይቤአዊ አገላለጥ ይመስለዋል። እንዴት ድንቅ ስዕል ነው! ገለባ ለሰው ሆድ ምግብነት የለውም። አይበላም። ከተበላ ግን ሆድ መሙላቱ፥ ከዚያ በኋላ ግን ጉዳት ማስከተሉ አይቀርም። መቸም ውፍረትና ጥንካሬ እንደማይሆን የተረጋገጠ ነው። በዘመናችን የሚገኙ የሐሰት ነቢያትን ስናስብ በኤርምያስ ዘመን የነበሩትንና እላይ ያየናቸውን ባህርያት ያንጸባርቁና አያንጸባርቁ እንደሆነ በማስተዋል ልና ውቃቸው ያሻል።

## ሕዝቅኤል 13 በሙሉ

ምዕራፉ በሙሉ ስለ ሐሰተኞች ነቢያት ነው የሚናገረው። ጎልተው የሚታዩት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

- ከራሳቸው አመንጭተው ይናገራሉ። ከገዛ ልባቸው ትንቢት ይናገራሉ (ቁ፥2)፤ የገዛ መንፈሳቸውን ይከተላሉ (ቁ፥3)፤ እግዚአብሔር ሳይልካቸውም 'እግዚአብሔር ይላል' ይላሉ (ቁ፥6)።
- ሥራቸው ገለባ ወይም ጭድ የሌለውን ጭቃ በቅጥር ላይ መምረግን የመሰለ ነው (ቁ፥10-16)። ጭድ የሌለው ጭቃ ያገጠጠ ግድግዳን ለጊዜው ይሸፍናል፥ ምናልባት ያምርም ይሆናል። ነገር ግን ከግድግዳው ጋር አይጣበቅም፤ ሲደርቅና ነፋስ ሲመታውም





ይሰነጣጠቃል፥ ዝናብ ሲዘንብም ይረግፋል። የጊዜን ፈተና አያልፍም ማለት ነው። እንዲሁ ሐሰተኞች ነቢያት ጊዜያዊና ስሜታዊ መፍትሔ ሊሰጡ ይችላሉ። ቃሉ እንደሚል መራጊዎቹ ቅጣትን ይቀበላሉ።

- የጥንቆላ መከዳና ሽፋን የሚሠሩ ሴቶች አሉአቸው (ቁ፥18)። የነዚህ መሣሪያዎች ትክክለኛ ሥራ ምንነት ግልጽ ባይሆንም ተንባዮቹን ሐሴት፥ ዕረፍትና ሰላም ያላቸው የሚያስመስላቸውን ምቾት የሚያመለክቱ መደገፊያዎች ወይም በቀጥታ ከጥንቆላ ጋር የተያያዙ የመተት ዕቃዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። በብሉይ ኪዳን ማርያምንና ዲቦራን የመሰሉ የትንቢት ስጦታና የነቢይነት አገልግሎት የነበራቸው ሴቶች የመኖራቸውን ያህል የጥንቆላ ሥራ ሠሪዎችና ተባባሪዎች የነበሩ ሴቶችም ነበሩ። ሴቶች ከተፈጥሮ ስሜታዊነትና ድካም የተነሣ በመልካሙም ሆነ መልካም ባልሆነው ፈጥነው የሚወሰዱ ናቸው። ይህ በዘመናት ሁሉ የነበረና በዚህም ዘመን የሚታይ እውነት ነው። ሴቶች በጌታ ሥራ ግንባር ቀደምም ተሳታፊም የሚሆኑትን ያህል በስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶችም በዚያው መጠን ተዝቀው ይወሰዳሉ።
- የነዚህ ሰዎች ሌላ ባህርይ ለጭብጥ ገብስና ቁራሽ እንጀራ ሲሉ ሞት የማይገባቸውን መግደልና መኖር የማይገባቸውን ደግሞ በሕይወት ማኖር ነው (ቁ፥18)። ጭብጥ ገብስና ቁራሽ እንጀራ የሆድ ዋጋ ተምሳሌታዊ መግለጫዎች ናቸው። እነዚህ ተንባዮች የሞትና የሕይወት ያህል ክብደት ያላቸውን ነገሮች በእጃቸው ወስደው ለሆድ ዋጋ ብቻ ሲሉ ፍርዳቸውን ይሰጡባቸዋል።
- ሌላው በዚህ ክፍል የተጠቀሰ ባህርይ የጻድቁን ልብ በውሸት ማሳዘንና የኃጢአተኛውን እጅ ደግሞ ማበርታት ነው (ቁ፥6)። ጻድቁን ያሳዝናሉ፥ ውስጡን ስሜቱን፥ ነፍሱን መንፈሱን ይጎዳሉ። የኃጥኡን ግን እጁን ያበረታሉ። ለመጥፎ ሥራ ማነሳሳት ብቻ ሳይሆን ጉልበትም ይሰጡታል፥ ያስደርጉታልም።

በዚህም ዘመንም የሚታዩት ነገሮች ከሕዝቅኤል ዘመን ያልተለዩ ናቸው። ፈጥሮና በስሜት ተነድቶ መናገርና የሰዎችን ስሜትና ቀልብ ከፍ ማድረግ፥ በጊዜ ውስጥ ሲመዘኑ የሚወድቁና ነዋሪ ያልሆኑ ትንቢቶችን መናገር፥ ከጥንቆላ የሚመሳሰሉና የማይተናነሱ ነገሮችን ማድረግ፥ ትንቢትን ለሆድ መሙያና መኖሪያ ማድረግ በዝተው ይታያሉ። የነቢይ አቀባበል እየተደረገላቸው፥ ቦታ እየተሰናዳላቸው፥ ምግብና ሌሎችም ምቾቶች ሁሉ እየተጠበቁላቸው ከልዩ ክብካቤ ጋር ይስተናገዳሉ። ከዚህ አልፎም ዓይናቸው የሳሳለትን የሰው ንብረት ሁሉ በትንቢት እያሳበቡ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህንን. . . ለእገሌ ስጥ ይልሃል' እያሉ የሚዘርፉም ጥቂት አይደሉም።

## ማቴ. 7፥15-23 (2ጴጥ. 2፥1 ሐዋ. 20፥29)

*የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።*

*በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንት አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፥ ከቶ አላወቅኋችሁም፥ እናንተ ዓመጸኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።*

እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ በጌታ ኢየሱስም ዘመን ሐሰተኛ ነቢያት ነበሩ። እኒህም እንደ ቀድሞዎቹ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን የሚያከብሩ ናቸው። ከውጭ የበግ ለምድ የለበሱ ውስጣቸው ግን ነጣቂ የሆኑ ተኩላዎች ናቸው። ከሽፋናቸው ብቻ በቀር ከዚያ በታች ምንም በግነት የላቸውም። ይህ የበግ ለምድ የአገራችን ባሕታውያን እንደሚደርቱት አለባበስ ሳይሆን በጎቹን የመምሰል ውስጣዊ ጥበብ ነው። ሃይማኖታዊ እየመሰሉና እያስመሰሉ ግን በመንጠቅ ለዝና፥ ለሥልጣን፥ ለገንዘብ የሚሠሩ ሰዎች ናቸው። የክርስቶስን ክብር እየሸፈኑ ራሳቸውን የሚክቡ መሆናቸው አንዱ መታወቂያቸው ነው።

ከላይ እንደለበሱት መጎናጸፊያ የክርስትና መልኩ ብቻ እንጂ ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን በፍርድ ቀን የእርሱ ወገን ባለመሆናቸው ይገለጣል። እነዚህ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ሰዎች በጌታ ስም ትንቢት ተናግረዋል፥ አጋንንት አውጥተዋል፥ ተአምራትም ሠርተዋል። ነገር ግን፥ ስሙን በሚጠሩት ጌታ ዘንድ ያልታወቁ ነበሩ። በፍርድ ቀን 'ከቶ አላወቅኋችሁም' ይላቸዋል። ቃሉ ብዙዎች በችኮላና ባለማስተዋል እንደሚያነብቡት 'አላውቃችሁም' ሳይሆን <u>አላወቅኋችሁም</u> ነው የሚለው፤ በሁለቱ መሃል ትልቅ ልዩነት አለ። አላወቅኋችሁም ማለት በፍርድ ቀን ብቻ ሳይሆን እነዚያ ሰዎች ቀድሞም ለጌታ ሳይሆን ለራሳቸው ሲማስኑም በጌታ ያልታወቁ ነበሩ ማለት ነው።

በፍርድ ቀን የመዳናችን ጉዳይ የሚለየው በሥራችን ሳይሆን በግንኙነታችን፥ ማለትም፥ ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት ነው። የመዳናችን ጉዳይ እርሱን ማገልገላችን ሳይሆን የእርሱ መሆናችን ነው። ትንቢት መናገር፥ አጋንንት ማውጣትና ተአምራት ማድረግ ትልልቅ ነገሮች ናቸው። ይሁኑ እንጂ ሐሰተኞችም ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ትልቁን ፈቃዱን ሳይፈጽሙ እነዚህን ነገሮች ማድረግ





ይቻላል ማለት ነው። ይህ እንዴት እንደሚሆን ማሰብ የሚያስገርም ነው። ያስገርም እንጂ ወይም አይግባን እንጂ ግን ይሆናል። ከዚህ በፊት የነበሩትና ዛሬ ያሉት ወደፊትም የሚኖሩት ምልክቶችን የሚያደርጉ ሐሰተኞች ሁሉ ናቸው 'ከቶ አላወቅኋችሁም' የሚባሉት።

## ማቴ. 24፥11-24 እንዲሁም ማር. 13፥22-23

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በመጨረሻው ዘመን ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ተነስተው ብዙዎችን እንደሚያስቱ፥ ታላላቅ ምልክትና ድንቅም እንደሚያሳዩ ይናገራል። ሐሰተኞች ከዚህ ማስጠንቀቂያ በፊትም ነበሩ። በመጨረሻው ዘመን ግን በብዙ ተባዝተው ይገኛሉ። ብዙዎች ይነሣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። በመጨረሻው ዘመን መኖራቸው ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ሁሉ ልምድ ለመጠቀም፥ ማለትም፥ የተሳኩላቸውን ስልቶች ለመውሰድና ተሳስተው ያፈሩባቸውን ደግሞ ላለመድገም ዕድል ያገኛሉ። ከዚህና ከሰይጣን የመጨረሻ ዘመን አሠራር የተነሣ ብዙዎችን በእኩይ ሥራቸውና በስሕተት መንገድ አዝሉና አግተልትሉ ለመሄድ የተመቸ ሁኔታ ይሆንላቸዋል።

በቁጥር 24 ላይ እንደምናገኘው እነዚህ ሰዎች ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን ያሳያሉ፤ ይህም ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ነው። 'ቢቻላቸውስ' ስለሚል ይህ የማይሳካላቸውና የማይሆንላቸው ነገር መኖሩን፥ ማለትም፥ የተመረጡት እንደማይስቱላቸው እንረዳለን። 'ክርስቶሶች' ስለሚልም በመጨረሻው ከሚነሣው 'የክርስቶስ ተቃዋሚ' ከሚባለው ሐሳዊ መሢህ ወይም ሐሰተኛ ክርስቶስ ሌላ 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ የሚነሡ በርካታ ሰዎች ይኖራሉ ማለት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክና በዘመናችንም የታዩና የተሰሙ ታሪኮች የዚህ አስረጅዎች ናቸው። በአውሮጳና በሰሜን አሜሪካ በርካታዎች ተነስተው ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት በአፍሪቃም በኬንያ አንዱ ብዙ የተነገረለት ክርስቶስ ነኝ ባይ ተነሥቶ ነበር። ይህ ሰው እግዚአብሔር የኬንያውያንን ኃጢአት ለማስተስረይ እንድሞት አመልክቶኛል ብሎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፥ እጅግ ተሰቃይቶ ነበር የሞተው። በ3ኛው ቀን ግን አልተነሣም። ይህ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜም ሌላ ክርስቶስ ነኝ ባይ እዚያው ኬንያ ውስጥ ከብዙ ተከታዮቹ ጋር በሕይወት ይገኛል። በቅርብም ባይሆን በአገራችንም በ16ኛው መቶ በዐፄ ዘድንግል ወይም ዳግማዊ አጽናፍ ሰገድ ዘመነ መንግሥት እንዲህ ያለ ሰው

ተነሥቶ ነበር፤ ሲጠየቅም ሲመርረመርም ነኝ ማለቱን አልካደም። ይህም ሰው በመጨረሻ ተገደለ።[1]

በማርቆስ 13 የተጻፈው ክፍል 'እናንተ ግን ተጠንቀቁ' ይላል። ክርስቲያኖች ይስታሉ? ወይም ሊስቱ ይችላሉ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው፤ በትክክል ሊስቱ ይችላሉ። የማይስቱ ቢሆኑ በጣም ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ስለምን ተሰጡ? ክርስትና ማለት በቀላሉ ማመንና መወሰድ ማለት ባይሆንም ብዙዎች ካለመማር የተነሣ በቀላል ይወሰዳሉና ማስጠንቀቂያው ሊበዛ የተገባ ነው።

## ሉቃ. 6፥26

*ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲህ ያደርጉላቸው ነበርና።*

በብሉይ ኪዳን ዘመን ነገሥታቱን የሚከቡትና በሕዝቡ ምኞትም የሚወሰዱ አንዳንድ ሐሰተኛ ነቢያት መልካም ይነገርላቸውና ከፍም ይደረጉ ነበር። ይህን በሰፊው ከላይ የተመለከትነው ሲሆን እዚህ እንደገና መጤን ያለበት አንድ ነገር የሰዎችን ሙገሳ ማግኘት ብቻውን የእውነተኛነት ምልክት ያለመሆኑ ነው። መሳሳታቸው ቆይቶ ገሃድ የሆነባቸው ብዙ ሐሰተኛ መሪዎች አያሌ ተከታዮች ነበሩአቸው። በቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው። ሰዎች አጨበጨቡልን ማለት በእግዚአብሔር ዘንድ ተፈትነን እውነተኛ ሆነን ተገኘን ማለት አይደለም። ማንም መሪ ለእኩይ ዓላማም ተነሥቶ በርካታ ተከታዮች ማሰለፍ ይችላልና አንድ አስተማሪ ወይም ሰባኪ አድናቂዎች ስለኖሩት ብቻ ትምህርቱ ንጹህ ነው ካልን ተሳስተናል። ሰይጣንም ራሱ እንኳ በቅዱሱ ፈጣሪው ላይ ተነሥቶ ሲያምጽ ተከታዮች አላጣም። በተለይም በየዋኀና በቀላሉ አማኝ በሆነ ማኀበረሰብ ውስጥ ይህን መሰል መንጋ ማግኘት ከባድና አድካሚ አይደለም። በጌታ አገልግሎት ዘመን እንዲህ የመሰሉ ሰዎች ነበሩ። ጌታ ግን ወዮላችሁ አላቸው። እንዲህ የመሰሉ ሰዎችን ዝም ማለት ወይም ስለእነርሱ መልካምን ፈልጎ መናገር ማለት እነርሱን ለማወፈር መመገብ ነው፤ መቀለብ።

## 2ቆሮ. 2፥17

*የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎች አይደለንምና።*

[1] ተክለ ጻድቅ፥ ገጽ 119።





በጳውሎስ ዘመን በቆሮንቶስና በሌሎችም ከተሞች የእግዚአብሔርን ቃል የሚሸቃቅጡ ሰዎች ነበሩ። እንዲያውም ብዙዎች ነበሩ። ጳውሎስ ራሱንና አብረውት የሚሠሩትን ከእነዚህ ሰዎች ጋር ካወዳደረ እነዚህም ሰዎች ክርስቲያኖችና የቃሉ አገልጋዮች ናቸው ማለት ነው። የእነዚህ ሰዎች ትልቅ ስሕተት ቀላቅሎ መሸቃቀጥ ነው። በአማርኛ ትርጉም ቃሉ ሁለት ቢሆንም አሳቡ ግን አንድ ነው።

አዲስ ኪዳን በተጻፈበት የመጀመሪያ ቋንቋ ቀላቅሎ መሸቃቀጥ ወይም καπηλεύοντες የሚለው ቃል ካፔሉዎ καπηλεύω ከሚል አንድ ስር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ለትርፍ ሲሉ የሆነውን ካልሆነው ጋር አደባልቆ ወይም አቅጥኖ መቸርቸር ማለት ነው። በንግድ ዓለም በተለይም በችርቻሮ ንግድ ትልቁ ነገር ትርፍ ወይም ገንዘብ ነው። ትርፍ ለማግኘት ከመጠን በላይ የሚጓጉ ቸርቻሪዎችም በሚሸጡት ነገር ውስጥ ያንን የሚመስል ሌላ ርካሽ ነገር ይጨምራሉ። አንዳንዶች የሚጨምሩት መናኛና ርካሽ ይሁን እንጂ ተመሳሳይ ነገር ነው የሚጨምሩት። አንዳንዶች ግን ያንን የሚመስል ጎጂም ነገር ይጨምራሉ። ለምሳሌ፥ ስንዴ ውስጥ እንክርዳድ፥ ጤፍ ውስጥ አሸዋ ይጨምራሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ በእግዚአብሔርም ቃል ውስጥ ለተለያየ ጥቅም ብቻ ሲሉ የራሳቸውን ነገር ወይም የእግዚአብሔር ያልሆነውን ወይም የሚመስለውን የሚጨምሩ አሉ። ጥቂት ከዚህ ጥቂት ከዚያ እያደረጉ የተምታታ ነገርን ይናገራሉ። ሙሉውን የእግዚአብሔርን ቃል አያስተምሩም። ይህም ማለት፥ ሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍን አያስተምሩም። ቆንጽለው ያወጣሉ፤ ሲያወጡም ያወጡትን ዐውደ ገብ በሆነ መንገድ፥ ማለትም ከምዕራፉ ወይም ከመጽሐፉ ወይም ከጸሐፊው ቀዳሚ አሳብ አንጻር ሳይሆን ለሰው ጆሮ ወይም ለራሳቸው ግብ እንደሚመች አድርገው ቁንጽሉን አሸብርቀው ያቀርቡታል። ግባቸው ጥቅምና ትርፍ እንጂ የቃሉን ትክክለኛ መልእክት ማስተላለፍ አይደለም። ለእነዚህ ቃሉን መስበክ ማትረፊያ ነው። እግዚአብሔርን ሊመስሉ ሲሞክሩም ለማትረፊያ ነው 1ጢሞ. 6፥5-10።

## 2ቆሮ. 11፥4

*የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ፥ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ በመልካም ትታገሡታላችሁ።*

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ቁጥር 3 ላይ እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት ይናገርና በቆሮንቶስም ቤተ ክርስቲያን የሔዋን አሳብ እንደተበላሸ ሁሉ ቅንነታቸውና ንጽሕናቸው እየተበላሸ መሆኑን በመጠራጠር ፈርቶአል። ቅን የሆነ አገልጋይ የሚያገለግላትን ቤተ

ክርስቲያን በንጽሕና ጠብቆ ለክርስቶስ ሊያቀርብ እንደሚመኝ ተመኝቶአል። እነዚህ የቆሮንቶስ ምዕመናን ግን ሔዋን የአሳቹን ድምጽ እንደሰማችና እንደተታለለች እየሰሙና እየተታለሉ ያሉ ይመስላሉ።

የተሳሳተ መንገድን የሚያሳዩአቸውን አሳቾች እየታገሡ ይሰሙአቸዋል፥ ይቀበሉአቸውማል። ዝም ከተባሉና በትዕግሥት ከታለፉ ያኔም ዛሬም እነዚህ ሰዎች የሚያቀርቡት እውነተኛ መሳይ ግን የእውነት ተቃራኒ ነገሮችን ነው። ለቆሮንቶስ ምዕመናን ያቀረቡት በጳውሎስ የተሰበከላቸውንና የተቀበሉትን ሳይሆን የፈጠሩትን ሌላ ኢየሱስ፥ የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስን ሳይሆን ልዩ መንፈስ፥ የእግዚአብሔር የማዳን መንገድና ኃይል የሆነውን ወንጌል ሳይሆን ልዩ ወንጌል ነው። ከቅዱስ ቃሉ ያፈነገጡ ማና ቸውም ነገሮች የተሳሳቱና የሚያሳስቱ ስለሆኑ ትምህርቶቹንም ሆነ አስተማሪዎቹን ላለመቀበል መጠንቀቅ አለብን። እንዲህ ያሉ ሌላ ወንጌል አቅራቢዎች የታወጀባቸውን ፍርድ በገላ. 1፥6-9 ተጽፎ እና ገኛለን። ጳውሎስ በዚህኛው ክፍል፥ 'እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን' ይላል። ጳውሎስ ራሱም፥ 'በፊት ተሳስቼ ነበር እውነተኛው ወንጌል ይህኛው ነው' ቢላቸው እንኳ እንዳይሰሙት ማስጠንቀቁ ነው። ይህን የሚሰብከው ከሰማይ የወረደ መልአክም እንኳ ቢሆን እሱም የተረገመ ይሁን ይላል። የሚያሳዝነው የቆሮንቶስ ምዕመናን እንዲህ ያሉትን ይታገሡ ነበር። ይህ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ትዕግሥት ሳይሆን የስንፍና የዋኅነት ነው።

## **ቆላ**. 2፥8-23

በዚህ ሰፋ ያለ ክፍል ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ሁለት ጠንካራ መሳሪያዎች ተጠቅሰዋል። እኒህም የሰው ወግና የዓለማዊ የመጀመሪያ ትምህርት ፍልስፍና ናቸው። 'እንደ ሰው ወግ' ሲል የክርስቶስን ትምህርት የማይከተል መሆኑን መግለጡ ነው። ይህ ለሰው አዕምሮ፥ ለሰው ስሜት፥ ለሰው ሥጋ፥ ለሰው ወግና ልማድ፥ ወይም ለማኅበራዊ ምቾት የሚስማማ ትምህርት ነው። ትምህርታቸው ለጌታ ቃል ታማኝ ከመሆን ይልቅ ለሰብአዊ ነገር የሚጠነቀቅና ሁኔታዎች በሚፈጥሩት ውጤት ጥሩ ወይም መጥፎ መሆን የሚደገፍ ነው። ለሁሉ ቦታና ለሁልጊዜ ከሚሆነው መለኮታዊ እውነት ይልቅ ለወቅቱና ለቦታው ተስማሚ በሆነ ሁኔታዊ ስነ ምግባር ወይም 'Situational Ethics' የሚባለውን መርኅ የሚመረኮዝ ነው።

እንደ ዓለማዊ መጀመሪያ ትምህርት ያለ ፍልስፍና የአዲስ ኪዳን ቋንቋ በሆነው በግሪክ እስቶይኬያ ቱ ኮስሙ፥ στοιχεῖα





τοῦ κόσμου የሚባለው እስቶኢኪዝም ወይም ስቶዪሲዝም (Stoicism) ከሚባል ፍልስፍና ጋር የተያያዘ ትምህርት ነው። የዚህን ፍልስፍና ምንነት በትንሹ መመልከት አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ የፍልስፍናውን ትምህርት ቀጥሎም የጥሬ ቃሉን ትርጉም እንመልከት።

የመጀመሪያው በሐዋ. 17፥18 ላይም የተጠቀሰው አንድ የፍልስፍና ቡድን ነው። በአቴና ጳውሎስ ባገለገለ ጊዜ የተጠቀሱት ኤፊቆሮሶችና ኢስጦኢኮች በጊዜው ከታወቁት ፍልስፍናዎች መካከል ሁለቱ ናቸው። ኤፊቆሮሶች የኤፊቆሮስ ወይም ኤፒክዩረስ ተከታዮች ሲሆኑ ዋና ትምህርታቸው የሕይወት ተቀዳሚ ግብ ደስታን መሻትና እርካታን መፈለግ ነው የሚል ነው። ኢስጦኢኮች ደግሞ በተቃራኒው እንዲህ የሚል ትምህርት አላቸው፤ አሳብ ከስሜት በላይ ነውና ስሜቶቻችን ተጨቁነው መገዛት አለባቸው፤ ደግሞም ከአመክንዮ እና ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተን መኖር አለብን ይላሉ። ሁለቱም ፍልስፍናዎች የተፈጥሮና የዓለም ሕግጋት የሚሉአቸውን ስሜትንና አስብን ማወቅና በእነርሱም መመራት አለብን በሚለው ትምህርታቸው ይስማማሉ። ኢስጦኢኮች ስሜትን ሲጨቁኑ ሥጋንም አብረው ነው የሚጨቁኑት፤ ሥጋዊነትን ሳይሆን ሥጋን ራሱን። በጣም ሲርቁ መብላትን፥ መልበስን፥ ማግባትንም ያጥላላሉ፥ አንዳንዴም ይከለክላሉ።

በጥሬ ቃሉ ትርጉም ከሄድን ደግሞ እስቶይኬዮን ወይም እስቶይኬያ የተፈጥሮአዊው ዓለምም ሆነ የማናቸውም ዓለማዊና ሃይማኖታዊ ትምህርት የመጀመሪያ ንጥረ ነገር ማለት ነው። ጤና ማውን የትምህርትነቱን ይዘት በተመለከተ በአዲስ ኪዳንም ቃሉ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ገላ. 4፥3 እና 9፤ ቆላ. 2፥8 እና 20፤ ዕብ. 5፥21 እንዲሁም ሐዋ. 21፥24። እንደ ግስ ሲወሰድም ቃሉ ራስን በአንድ ዓይነት መሠረታዊ ሕግ ወይም ትምህርት ውስጥ መጠበቅና መምራት ማለት ነው፤ ሐዋ. 21፥24፤ ገላ. 5፥25 እና 6፥16፤ ሮሜ. 4፥12፤ እንዲሁም ፊል. 3፥16።

ሕግ ወይም መመሪያ በራሱ ስሕተት አይደለም። ስሕተት የሚሆነው ግን አስተማሪዎቹ የሚያወጡአቸውን ሕግጋትና መመሪያ ደንቦች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል ሥልጣን ስለሚሰጡአቸው ነው። በቆላስይስ ምዕራፍ ሁለት ጳውሎስ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ ስንመለከት በቁጥር 8 የሰው ወግ፥ የዓለማዊ መጀመሪያ ትምህርት እንዲሁም ፍልስፍና፤ ከቁጥር 11 እስከ 15 የተለያዩ መንፈሳዊ የሚመስሉ ነገር ግን ከሙላት ወይም ሙሉ ሰው ከመሆን የሚያርቁ ስርዓቶች፤ ከ16 እስከ 23 ደግሞ አንድ ሰው ፍጹም ሊሆን ቢፈቅድ እነዚህን የተለያዩ ሕግጋት ተጨንቆና ተጠቦ መጠበቅ አለበት የሚል ትምህርትን ይሰጣሉ። በአንክሮ ሲመለከቱአቸው እነዚህ ነገሮች የአማኝና የክርስቶስን ግንኙነት የሚገነቡ ሳይሆኑ ከውጪ የሚታዩና ያንን ሰው ለመለካት ሆን

ተብለው የተሠሩ ድንጋጌዎች ናቸው። በዘመናችን የስሕተት አስተማሪዎችም ዘንድ የምናገኛቸው በርካታ ድንጋጌዎችም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

## 1ጢሞ. 1፥3-4 እና 4፥1-5

ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊዜ፥ ለአንዳንዶች ልዩ ትምህርትን እንዳያስተምሩና ወደ ተረት መጨረሻም ወደሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ እንዳያደምጡ ልታዛቸው በኤፌሶን ተቀመጥ ዘንድ ለመንሁህ፤ እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮች ክርክርን ያመጣሉና፥ በእምነት ግን ላለ ለእግዚአብሔር መጋቢነት አይጠቅሙም።

መንፈስ ግን በግልጥ፥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፥ እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፥ አምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ። እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፥ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነው።

በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንም የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን ችግር የመሰለ ሳይፈጠር አልቀረም። በዚህችም ቤተ ክርስቲያን አንዳንዶች መጨረሻ የሌለውን የትውልዶች ታሪክን መንደርደሪያ እያደረጉና የፈጠሩትንም ተረት እያወሩ የስሕተት ትምህርት ማስተማር የጀመሩ ይመስላል። እንዲህ የመሰለው ተረት ከብሉይ ኪዳንም ታሪክ የተወሰደና የተጨመረበት ቢሆንም ወይም ቢመስልም እንኳ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደተናገረው ውጤቱ ክርክርን ማምጣት ነው። ክርክር ደግሞ በቃሉም ላይ ቢመረኮዝ እንኳ እውነትን ከማወቅ ይልቅ ለማሸነፍ የሚደረግ ትግል በመሆኑ ቃሉን ለማጥና ት የምናውለውን ጊዜና ስሜት ይወስድብናል። ሕይወትን ከሚለውጠው የክርስቶስ ትምህርትም ፈቀቅ ያደርገናል።

በዘመናችንም እንዲህ የመሰሉ እጅግ የበዙ በሰዎች የተፈጠሩ ተረቶች አሉ። አንዳንዶቹ ስለ ክርስቶስ የሚናገሩና የሚጠቅሙ መስለው የተሠሩ ናቸው። ለምሳሌ፥ ጌታ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት ስለኖረባቸው የሕፃንነትና የወጣትነት ወራት አስመልክቶ የተጻፉ ተረት መሰል ነገሮች አሉ። እኒህ ጽሑፎችና ትምህርቶች አንደኛ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ከቦታውም ከዘመኑም እጅግ ርቀው የተጻፉ፤ ሁለተኛም በሰዎች ውስጥ የተነሱ ጥያቄዎችን ከሰው አዕምሮ በመነጩ ግምቶች ለመመለስና በአዲስ ኪዳን የታየ የመሰለ ክፍተትን ለመሸፈን የተፈጠሩ ተረቶች ናቸው። ደግሞም የሰዎች ስነ ልቡና ለተረትና ለትንግርት ምቹ በሆነባቸው የአፈ ታሪክ ዘመናት መጻፉቸው ሌላው ችግራቸው ነው። እኒህ ለታሪክነትም ለደኅንነትም የማይጠቅሙ ተረቶችና አፈ ታሪኮች ግን





ብዙዎችን መስጠው ወስደዋል። በተለይም የእኛን መሰል ስነቃል ወዳድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚያደርሱት አደጋ ከፍተኛ ነው።

በምዕራፍ አራት ኋለኞች ዘመናት ብሎ ጳውሎስ የጠቀሰው እኛ ያለንበትንና የሚመጣውን ዘመናት ብቻ ሳይሆን በራሱ ዘመን እየሆኑ ያሉ ስህተቶችን ስለጠቀሰ ያንንም ጊዜ የጨመረና እስከ ጌታ ምጽአት ድረስ ያለውን ጊዜም ያካተተ ነው። ይህ መልእክት በሚጻፍበት ጊዜ ጢሞቴዎስ በኤፌሶን እያገለገለ ነበረ። ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ሲያልፍ ጢሞቴዎስን በኤፌሶን ትቶ ማለፉ የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎችን ይከላከልም ዘንድ ነው።

በኤፌሶን የነበረው ስሕተት በቆላስይስ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ነው። እነዚህም ሰውነትን ርኩስ አድርገው የሚመለከቱ፥ ምግብንና ጋብቻንም የሚከለክሉ የቀደሙ የሐሰት ትምህርቶችን የሚያስተጋቡ ናቸው። እነርሱ ‘ሥጋዊ’ ናቸው ብለው የሚጠሩአቸውን እነዚህን ነገሮች መከልከላቸው መንፈሳዊ ሊያስመስላቸው ይችል ይሆናል። በኛም ባህል ጉስቁልና ወይም ከምቾት መራቅና መንፈሳዊነት ባለመስተዋል ሞክሼ ሆነው ኖረዋል። በአንዳንድ ሃይማኖቶች እንዲሁም የስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች ዘንድ መሪዎቹም ሆኑ ተከታዮቻቸው እኒህን የመሰሉ አካላዊና ስሜታዊ ዋጋን የሚጠይቁ ስርዓቶችን እንዲጠብቁ መገደዳቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች መንፈሳዊ ሊያስመስላቸው ይችላል። አንዳንዶችም ጽድቅ ዋጋ ማስከፈል አለበት ብለው ስለሚያምኑ ለመክፈል ራሳቸውን በአዕምሮ፥ በመንፈስም፥ በአካልም ሲያጎሳቁሉ ይኖራሉ። መታየት ያለበት ግን ከሽፋኑ ጠለቅ ያለው ይዘት ነው። ሜዳዊ ሥርዓታቸውንና የሚናገሩትን ነገር በስሱ ብቻ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ትምህርት ጋር መቃረን ያለመቃረናቸውንም መመልከት ይኖርብናል።

እነዚህ የስሕተት አስተማሪዎች ሃይማኖትን የሚክዱትና መልካም የሆነውን የሚከለክሉት ‘በገዛ ኅሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው’ ነው። ይህን አባባል ከሰውነታችን ሁኔታ ጋር አመሳስለን ብናየው እንዲህ ነው። የሰውነታችን አንድ ክፍል ሲቃጠል በተቃጠለው አካባቢ ያሉ የነርቭ አውታሮቻችን ጫፎች ተለብልበው ይበላሹና ምንም መልእክት የማይቀበሉና የማያስተላልፉ ይሆናሉ፤ ያም አካባቢ በድን ይሆናል። ከዚያ በኋላ የተቃጠለው አካባቢ መወጋት ወይም መቆረጥ ቢደርስበትም ቶሎ ምላሽ ለመስጠት አዳጋች ይሆንና ለከፋ አደጋ መጋለጥ ይከተላል። ጉልህ ጠባሳ ያለን ሰዎች ይህን በመንካት ማረጋገጥ እንችላለን። የነዚህ ሰዎች ግን አካላቸው ሳይሆን ሕሊናቸው ነው እንደሚቃጠል ወይም እንደተቃጠለ ያህል የደነዘዘው።

ሕሊና ባወቅነውና በተረዳንበት እውነት ላይ ጤናማ በሆነ አቅጣጫ እንድንሄድ የሚረዳን አቅጣጫ ጠቋሚያችን ነው። በድን ከሆነ ወይም ከደነዘዘ ግን ልክ የስሜት አውታሮቹ ጫፎች

የተጎዳበት ሰው የአካሉ ጉዳት እንደማይሰማው ሁሉ ይህም ሰው አቅጣጫ ሲስት፥ ከመስመር ሲወጣና ሲጠፋ፥ ሌሎችንም ሲያጠፋ መሳቱና ማጥፋቱ አይታወቀውም፤ ቅሬታም አይሰማውም። ብዙዎች የስሕተት አስተማሪዎች አውቀው ወይም ሳያውቁ ሕሊናቸውን ያደነዘዙ ሰዎች ናቸው።

## 1ጢሞ. 6፥3-10

*እነዚህን አስተምርና ምከር። ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሚሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት የማይጠጋ ቢሆን፥ በትዕቢት ተነፍቶአል አንዳችም አያውቅም፥ ነገር ግን ምርመራን በቃልም መዋጋትን እንደ በሽተኛ ይናፍቃል፤ ከእነዚህም ቅንዓትና ክርክር ስድብም ክፉ አሳብም እርስ በርስ መናደድም ይወጣሉ፥ አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እንደ እነዚህ ካሉት ራቅ። ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፥ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል። ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ።*

በዚህ ክፍል የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች ባህርያት በዝርዝር ተጽፈዋል። ቀደም ሲል ከተዘረዘሩ ባህርያት ውስጥ እንደ ክርክርና በቃል መዋጋት፥ ሳያውቁ ያወቁ መምሰልና የውስጥ የስነ ምግባር መበላሸት ናቸው። ከእንዲህ ያሉ ሰዎች ራቅ ይለዋል ጳውሎስ ጢሞቴዎስን። በዚህ ምንባብ ሁለተኛ አጋማሽ የተነገረው የስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች ጉልህ ባህርይ ፍቅረ ንዋይ ነው። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ለመምሰል ሲሞክሩ ዓላማ አላቸው። ያም እርሱን ለመምሰል ሳይሆን ለመምሰል ሞክሮ ወይም መስሎ ገንዘብ ማግኘት ነው። ይህ ማስመሰል እንጂ መምሰል አይደለም።

ገንዘብ በራሱ ጥፋትና ክፋት የለውም። በአግባቡ ከተያዘ ገንዘብ ጥሩ አገልጋይ ነው። ለማናቸውም ክርስቲያናዊ አገልግሎትም ተፈላጊ ነገር ነው። ግንኙነቱ ከአግባቡ ውጭ ከሆነና ስሜታዊ መተሳሰር ከታከለበት ግን ገንዘብ በጥሩ አገልጋይ ፈንታ ክፉ ጌታ ይሆናል። 'የክፋት ሁሉ ሥር' የተባለው ገንዘብ ራሱ ሳይሆን ገንዘብን መውደድ ነው። እግዚአብሔርን መውደድና ገንዘብን መውደድ ወደ ምርጫ ከመጡ ገንዘብ እንደ አምላክ ሊሆን ይችላል። ጌታ በማቴ. 6፥24 እንዳስተማረውም መራጩ ከሁለት ጌቶች አንዱን ለመምረጥ ይገደዳል። ከሁለቱ ጌቶች የቱ እንደሚገዛን ለማወቅ አሳባችንን፥ ጊዜያችንንና ጉልበታችን የሚወስደው የቱ መሆኑን ማወቁ በቂ አመልካች ነው።





አንዳንድ አገልጋዮችና አገልግሎቶች ከገንዘብ ጋር ያለልክ የተጣበቁ ናቸው። አገልግሎቱ አገልግሎት ሳይሆን ንግድ፥ እነርሱም አገልጋይ ሳይሆኑ ቀራጭ ይመስላሉ። ገንዘቡ ከሌለ አገልግሎቱም አይኖርም። የብልጽግና ወንጌል ሰባክያን ዋና ወጥመድ ይህ ነው። ይህን ማወቅ ከስሕተት አሠራር ጋር ምን ያህል የተጣበቁ መሆናቸውን ያሳያልና ከንዋይ ጋር የተቆራኙ አገልጋዮችን ጠንቅቆ ማወቁ አስፈላጊ ነው።

## 2ጢሞ. 2፥16-18

*ነገር ግን ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ፤ ኃጢአተኝነታቸውን ከፊት ይልቅ ይጨምራሉና፥ ቃላቸውም እንደ ጭንቀር ይባላል፤ እነርሱም ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ናቸው፤ እነዚህም፥ ትንሣኤ ከአሁን በፊት ሆኖአል እያሉ፥ ስለ እውነት ስተው፥ የአንዳንዶችን እምነት ይገለብጣሉ።*

የሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ትምህርት ትንሣኤን መካድ ሳይሆን የትንሣኤን ትምህርት ማጣመም፥ ማለትም፥ ከአሁን በፊት ሆኖአል፥ ተፈጽሞአል የሚል ነው። ሄሜኔዎስ በ1ጢሞ. 1፥20 ተጠቅሶአል። በዚህ ስፍራ ይህ ሰው እምነትን በተመለከተ ኅሊናን ጥሎ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ የጠፋ ሰው መሆኑ ተገልጦአል። ከእምነት ስቶ ሌሎችንም የሚያስት ሰው ነው። የነሄሜኔዎስ ትምህርት ሰው ሲድን ወይም ሲያምን ከሞት ተነስቶአል፤ ትንሳኤ ያ እንጂ ሌላ አይደለም፤ ከዚህ በኋላ የሚሆን አካላዊ ትንሣኤ የለም ይላሉ። ጠቅላላው አዲስ ኪዳን ግን የዚህን ስሕተት ይገልጣል፤ በጥቂቱ 1ተሰ. 4፥ 1ቆሮ. 15፥ እና 2ቆሮ. 5 አካላዊ ትንሣኤ መኖሩንና ያም ወደፊት አንድ ቀን እንደሚሆን ይናገራሉ።

ትንሣኤ ከአሁን በፊት ወይም ስንድን ሆነ የሚሉ አስተማሪዎች አሁን በትንሣኤ አካል ነን ሊሉን ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የትንሣኤን በረከቶች ሁሉ ልንለማመድ ግድ ሊሉን ነው፤ የትንሣኤ አካል ስለማይታመም ላንታመም፥ ስለማይሞትም ላንሞት ነው ማለት ነው? እንዲህ የሚሉ አስተማሪዎችም አልታጡም። ከ30 ዓመታት በፊት በአገራችን ማደግ ጀምሮ የነበረ አርነት እየተባለ የሚጠራው እምነት አንድ ትምህርቱ ክርስቲያን መሞትም እንደማይኖርበት ነበር። እንደዚያ እያሉ የሚያስተምሩ አስተማሪዎቻቸው ሲሞቱ እያዩ የማይማሩ የዋኅ ተከታዮች ደግሞ ጥቂት አይደሉም። ከዚህ በፊት እንደተከሰተው ሁሉ የዚህ ዓይነት ትምህርት በቅርብ ወይም በሩቅ ሊከሰት ስለማይቀር መጠንቀቁ መልካም ነው።

## ቲቶ. 1፥10-16

> የማይታዘዙና ከንቱ የሚናገሩ የሚያታልሉም ይልቁንም ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ ብዙ ናቸውና፤ እነዚህም ስለነውረኛ ረብ የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን በሞላው ስለሚገለብጡ፥ አፋቸውን መዝጋት ይገባል። የገዛ ራሳቸው ነቢይ የሆነ ከእነርሱ አንዱ፥ የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸተኞች፥ ክፉዎች አራዊት፥ በላተኞች፥ ሥራ ፈቶች ናቸው ብሎአል። ይህ ምስክር እውነተኛ ነው። ስለዚህ ምክንያት የአይሁድን ተረትና ከእውነት ፈቀቅ የሚሉትን ሰዎች ትእዛዝ ሳያዳምጡ፥ በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው። ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው፤ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፥ ነገር ግን አእምሮአቸውም ሕሊናቸውም ረክሶአል። እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ስለሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል።

ይህ ክፍል ስለ ሽማግሌዎች መለኪያ ከተናገረና ሽማግሌዎች ተቃዋሚዎችን ሊወቅሱ የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው ከተናገረ በኋላ 'ከተገረዙት ወገን' የሚሆኑ ስለተሰኙት ሰዎች ይናገራል። እነዚህ የማይታዘዙና፥ ከንቱን የሚናገሩ የሚያታልሉም ሰዎች የሆኑ አይሁድ አድራጊዎች *(Judaizers)* ወይም ሰዎችን ወደ ይሁዲነት ለመለወጥ ታጥቀው የተነሡ ገያሪዎች *(Proselytizers)* ናቸው። መገየር ወደ ሕገ ኦሪት ሰዎችን መለወጥ ወይም ማሳመን ነው። ቀደም ባለው የብሉይ ኪዳን ዘመንም ሆነ በኋላ በነበረው ጊዜ ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው በዘር አይሁድ ባይሆንም በሃይማኖት ይሁዲ ሊሆን ቢወድ ሊፈጽማቸው የሚጠበቁበት ስርዓቶች አሉ። እነዚያን ከፈጸመ ያ ሰው አይሁዳዊ እንደሆነ ይቆጠራል። በክርስትና ዘመን የመጀመሪያ ወቅትም እንደዚህ የሚያደርጉ ክርስቲያን አይሁድ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች አንድ ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት መገረዝንና ሌሎችም የአይሁድ ሥርዓቶችን መጠበቅ አለበት የሚሉ ናቸው። አንዳንዶቹ ከክርስትና አገልጋዮች ይልቅ የአይሁድ እምነት ጠበቆች ናቸው። በፊል. 2፥9-15 ጳውሎስ ከሐሰተኛ መገረዝ እንዲጠበቁ የጻፈው ከአይሁድ ሃይማኖት ጋር ስለተያያዘው ግዝረት ሲናገር ነው።

በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት ክርስትናን ራሱን ከአይሁድ የእምነት ቡድኖች እንደ አንዱ፥ ለምሳሌ እንደ ፈሪሳውያን ወይም ኤሲናውያን አድርገው የሚመለከቱ ብዙዎች ነበሩ። እኒህ ሰዎች የአይሁድን እምነትና ወግ ለመጠበቅ ሲሉ፥ ማለትም ለክርስትና ሳይሆን ለአይሁድ ሃይማኖት፥ ልማድና ወግ ሲሉ ዘብ ይቆማሉ። የአሕዛብን አብያተ ክርስቲያናት ያወከውን ይህንንና የመሳሰሉትን ወጎች በማንገሣት የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ በጉዳዩ መክሮ ውሳኔ እስኪሰጥ አድርሰውት ነበር፤ ሐዋ. 15። ምክርና ውሳኔውም ከተደረገ በኋላ እንኳን ወግን በማጥበቅ ቤተ ክርስቲያንን ያወኩ ሰዎችም ነበሩ።





አውቀው የሚያሳስቱ አንዳንዶች ቢኖሩም እንኳ ከእነዚህ ብዙዎቹ ስተው የሚያሳስቱ ናቸው። እነዚህ የተሰጣቸውንና የሰሙትን ከቃሉ ትምህርት ጋር ይስማማ ወይም አይስማማ እንደሆነ ሳያረጋግጡ በጆሮአቸው የሞላውን በአፋቸው አሸንዳ ያፈሱት ነበር። አንዳንዶቹ ደግሞ በቁጥር 11 እንደተጻፈው አውቀው የማይታዘዙ፥ ከንቱን የሚናገሩና የሚያታልሉ እንዲሁም ለነውረኛ ረብ ሲሉ የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን የሚገለብጡ ናቸው። ይህ ነውረኛ ረብ የተለያየ ነገር ሊሆን ይችላል። ገንዘብ፥ የማኅበር መሪነት ወይም ሥልጣን፥ ከማኅበሩ ኀልውና ጋር የተቆራኘና ማኅበሩ ከሌለ የማይኖር የግል ጥቅም፥ ሌላም እሱን መሰል ነገር ሊሆን ይችላል።

በቁጥር 12 ላይ ጳውሎስ የራሳቸው የሆነ ሰው ስለዚህች ከተማ ሰዎች የተናገረውን ይጠቅሳል። ይህ ሰው ምናልባት ኤፒሜኒደስ የተባለው በ6ኛው መቶ ዓመተ ዓለም የነበረ ቀርጤሳዊ ፈላስፋ ነው ተብሎ ይታመናል። ይህ ሰው ስለነዚህ ሰዎች ባህርያት ሲናገር ውሸታምነታቸውን፥ ክፉ አራዊትነታቸውን፥ በላተኛ የሆነ ሥራ ፈትነታቸውን ተናገረ። የከተማዋ ሰዎች ሁሉ እንዲያ ናቸው ለማለት ባይቻልም ይህ በውስጥዋ ከነበሩት ገያሪዎች ወይም አይሁድ አድራጊዎችና ከስሕተት አስተማሪዎች ባህርይ ጋር የተመሳሰለ ነው።

በቁጥር 13 እና 14 አማኞችን ስለመውቀስ ሁለት ነገሮችን ይናገራል። የመጀመሪያው ፈቀቅ እንዲሉ ሁለተኛው ደግሞ ጤናሞች እንዲሆኑ ነው። እንዲርቁ የተናገራቸው ከሁለት ነገሮች ነው፤ ከአይሁድ ተረትና ከእውነት ፈቀቅ ከሚሉ ሰዎች ትእዛዝ። ጤናሞች እንዲሆኑ የተናገረው ደግሞ በሃይማኖት ወይም በእምነት ነው። ለጤናማ እምነት ከተሳሳተ ትምህርት ፈቀቅ ማለት ብቻውን በቂ አይደለም፤ ጤናማ የሆነውን ትምህርትም በጥንቃቄ መያዝ አስፈላጊ ነው። ዋናው መንገድ እንዲያውም በሸተኛውን ትምህርት አውቆ መሸሽ ሳይሆን ጤናማውን በጥንቃቄ መመገብ ነው። ትክክለኛውን የሚያውቅ ሐሰተኛው ሲመጣ በቀላሉ ሊለየው ይቻለዋል።

ቁጥር 15 እነዚህ የስሕተት አስተማሪዎች አእምሮአቸውና ሕሊናቸው የረከሰ መሆኑን ይናገራል፤ ሕሊናቸው ስለረከሰ ሁሉ ለእነርሱ ርኩስ ነው። ንጹሑንም ርኩስ ብለው ነው የሚጠሩት። ልክ ጆንዲስ የሚባል ዐይን ብጫ የሚያደርግ በሽታ የያዘው ሰው ወይም ባለ ብጫ መስተዋት መነጽር ያደረገ ሰው የሚያየው ነገር በሙሉ በስሱ ብጫ የፈሰሰበት መስሎ እንደሚታየው ሁሉ እነዚህ የተሳሳቱ አስተማሪዎችም ሁሉን በረከሰ አእምሮ ስለሚያዩት ሁሉ ርኩስ መስሎ ይታያቸዋል። በቁጥር 16 ደግሞ ሌላ አንድ ባህርያቸው ተጠቅሶ ይገኛል። እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፤ ነገር ግን አስጸያፊዎችና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም የማይበቁ ናቸውና በተግባራቸው ይክዱታል።

ትምህርታቸውን ብቻ ሳይሆን ሥራቸውንና ጠቅላላ ኑሮአቸውንም መመልከት አስፈላጊ ነገር የሚሆነው ስለዚህ ነው።

## 2ጴጥ. 2፥1-3 (ምዕራፉ በሙሉ)

ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ፥ እንዲሁም በመካከላቸው ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፉ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ፤ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል፥ በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል። ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፥ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም፥ ጥፋታቸውም አያንቀላፋም።

እነዚህ ጥቅሶችና ምዕራፉም በሙሉ የሐሰተኞች አስተማሪዎችን ኀልውናና ተጨማሪ ባህርያት ይገልጣሉ። ጴጥሮስ ሐሰተኞች ነቢያት ቀድሞም እንደነበሩ በዘመኑም ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሆነው እንደሚገኙ ጽፎአል። ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈበት ዘመን የመጀመሪያው ምዕት ዓመት አጋማሽ ገደማ ነው። በጌታ ዘመን እንደነበሩና ወደፊትም እንደሚኖሩ ጌታ ራሱ እንደተናገረ በጴጥሮስም ዘመን ታይተዋል። በዚህ ክፍል የተገለጡት ባህርያት፥

አንደኛው ክህደት ነው። ጌታን የሚክድ ትምህርት አላቸው። አምላክነቱን ወይም ሰውነቱን፥ ሥራውን ወይም ኃይሉን ይክዳሉ።

ሁለተኛ ፈጣን ጥፋትን በራሳቸው እየሳቡ አጥፊ ኑፋቄን አሹልከው ያስገባሉ። ኑፋቄ የሚለው ቃል በጥሬ ትርጉሙ የሚነፍቅ፥ የሚከፍል፥ የሚገምስ የስሕተት ትምህርት ማለት ነው። ጴጥሮስ 'አሹልከው' ይላልና የስሕተት ትምህርቶችን የሚያስገቡትም በይፋ ሳይሆን አሹልከው ነው። ይህ የሥራቸውን ምስጢራዊ ባህርይም ያመለክታል።

ሦስተኛው ሌሎችን እስኪስቡበትና የእውነት መንገድ እስኪሰደብ ድረስ ሴሰኞች መሆናቸውና አሳፋሪ ነውሮችን የሚያደርጉ መሆናቸው ነው። ቁጥር 14 እና 18 ይህን አሳብ ይበልጥ ያጎላዋል።

አራተኛ ገንዘብን በመመኘት በተፈጠረ ነገር በሰዎች ላይ ይረቡባቸዋል። የተፈጠረ ነገር እነርሱ ራሳቸው የፈጠሩት ትምህርት የሚመስል የፈጠራ ወሬ ነው። በዚህም የሰዎችን አእምሮ ይማርካሉ፤ ገንዛባቸውንም ይበዘብዛሉ። በቁጥር 15 እና 16 የተጠቀሰው በለዓም የተባለው ሰው የዓመፃ ገንዘብን የወደደ ሰው ነው። በዘኍ. 22 እስከ 24 የሚገኘውን ታሪኩን ይሁዳም በመልእክቱ ቁጥር 11 ጠቅሶታል። ለምዋርት ገንዘብ ብሎ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመርገም ብዙ መቶ ኪሎ ሜትር የተጓዘ ሰው ነበር። ለአገልጋዮች ገንዘብን መስጠት ትክክል ቢሆንም ከመስጠታችን በፊት አገልጋዩ የእግዚአብሔርን መንግሥት





እያገለገለ ወይም የራሱን ዝና እያስፋፋ እንደሆነና የምንሰጠው ገንዘብ ደግሞ ትክክለኛ የሆነውን የእግዚአብሔር ሥራ እንደሚያስፋፋ ወይም የሰውየውን ብቻ እንደሚያገንን መጠየቅና አርኪ መልስ ማግኘት አለብን። ይህ የ2ኛ ጴጥሮስ ሁለተኛ ምዕራፍ በሙሉ ከይሁዳ መልእክት ጋር በጣም የሚቀራረብ ነው። የይሁዳ መልእክት በሙሉው በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ቀርቦአል።

## 1ዮሐ. 2፥18-23

ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው፥ የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደሆነ እናውቃለን። ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ። እናንተም ከቅዱሱ ቀባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ። እውነትን የምታውቁ ስለሆናችሁ፥ ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም። ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው።

ዮሐንስ ዘመኑን የመጨረሻው ሰዓት ብሎ ይጠራዋል። ጌታችን መጀመሪያ ከመጣበትና ካረገበት ጀምሮ ዳግም እስኪመጣ ድረስ ያለው ጊዜ በሙሉ የመጨረሻው ሰዓት ወይም የመጨረሻው ዘመን ተብሎ ይጠራል። ዮሐንስ መልእክቱን የጻፈበትም ሆነ ዛሬ እኛ ያለንበት ጊዜ የመጨረሻው ዘመን ነው። ብዙዎች እንደሚመስላቸውና ተስፋ እንደሚያደርጉትም ከክርስቶስ ምጽአት በፊት ያለው የመጨረሻው ዘመን በበረከት ነዶ በነዶ የምንሆንበት ጊዜ ከመሆን ይልቅ ሰይጣናዊ ረቂቅ አሠራር እንደአሸን የሚፈላበት ነው። በመጨረሻው ዘመን ከሚሆኑት ክፉ ነገሮች መካከል ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች መውጣታቸው ወይም መነሣታቸው ነው። በዮሐንስ ዘመን ተነሥተው እንደነበር ባለፉት ዘመናትም እንደተነሡ ታሪክ ይመሰክራል። ዛሬም እንዲሁ ነው። ራእ. 13 እና 19 እንደሚነግረን ደግሞ የመጨረሻውና ዋናው ተቃዋሚ ገና ወደፊት ይነሣል።

ከጌታ ጋር የሆንን ሁሉ ከቅዱሱ፥ ማለትም ከእግዚአብሔር ቅባትን ተቀብለናል። ይህ የተቀበልነው ቅባት ለጥቂቶች የተቸረ ልዩ ሹመት ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለን ሁላችን የታደልነው እውነትን የማወቅና ስሕተትን የማስተዋል መረዳት ነው። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ አድሮ ስለሚመራን ውሸታቸውን ከእውነት ለመለየት አይሳነንም። የለየነውንና የተረዳነውን ያህል በቀላሉ ሊወሰዱ ለሚችሉ ለሌሎች ማስጠንቀቅ ይገባናል።

ኢየሱስን መሢሕ አይደለም ብሎ የሚክድ ከሐዲ አብና ወልድ የሌሉት እርሱ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። እንደነዚህ ያሉት ሰዎች በጥሩ ስም እየተጠሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ቢገኙም እግዚአብሔር ስለ ልጁ የገለጠውን እውነት አልተቀበሉምና የማያምኑ ሰዎች ናቸው። እንድንበት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ብቸኛ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህን መንገድ ያለመቀበል ትእዛዙን ያለመቀበል ነው፤ ትእዛዙን ያለመቀበል ደግሞ አዛዡንም ያለመቀበል ነው።

## 1ዮሐ. 4፥1-3

*ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።*

ዮሐንስ በመልእክቱ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና ሰውነት ደጋግሞና አጉልቶ ጽፎአል። ዮሐንስ ረዥም ዕድሜ የኖረና ከሐዋርያትም ሁሉ በኋላ የሞተ ሐዋርያ ነው። በረዥም ዕድሜው ብዙ ስህተቶችንም ያየ ምስክር ነው። ይህን መልእክት የጻፈው በመጨረሻ ሲያገለግል ከነበረበት ከኤፌሶን ሳይሆን አይቀርም። ይህ ከሆነ ጌታ ካገለገለበት ዘመን ወዲህ ከኀምሳ ዓመታት በላይ አልፈዋልና አሁን በቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ሁለተኛና ሦስተኛ ትውልድ ነው። ስለዚህ ለዚህ ጌታን በአካል ላላየ ትውልድ በአካልና በክብሩ ያየው ዮሐንስ ያየውን፥ የሰማውን፥ የዳሰሰውን አስረግጦ ይመሰክራል። በዚህም የጌታን ክርስቶስነትና በሥጋ የተገለጠ አዳኝነት ያብራራል።

አምላክነቱን ለማይቀበሉት ቀደም ብሎ በምዕራፍ ሁለት ተንትኖአል። አሁን ደግሞ በሥጋ መምጣቱን ይገልጥና ይህን መቀበልንና ያለመቀበልን የእውነትና የስሕተት መለኪያ ያደርገዋል። ቀደም ብለው ተጀምረው በዚህ ዮሐንስ ይህን በሚጽፍበት ዘመን ስር የሰደዱ ሁለት ትምህርቶች ነበሩ። እነዚህም ዶሴቲዝም እና ግኖስቲሲዝም ወይም ኖስቲሲዝም ይባላሉ። ሁለቱም የተለያዩ ቢሆኑም የሚመሳሰሉባቸው አንድ ነገር ነው፤ ይኸውም መንፈስና መንፈሳዊነትን በማጉላት ሥጋና ከሥጋ ጋር የተያያዘ ማናቸውንም ነገር ማጥላላት ነው። ከዚህ የተነሣ ጌታ ክርስቶስ በሥጋ ተገለጠ የሚለውን ትምህርት አይቀበሉም። ስለዚህም ይመስላል ዮሐንስ በሥጋ መገለጡንም በዚህ ስፍራ የሚያጎላው። መናፍስትን ሁሉ መመርመር እንዳለብንና ከመመርመሪያዎቹ ነጥቦች አንዱ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ መቀበል ነው። የክርስቶስ ሙሉ አምላክና ፍጹም





ሰው መሆን በክርስትና እምነት ውስጥ አንጓ የሆነ አስተምህሮ ነው።

የክርስቶስ አምላክነትና ሰብነት ገና ከመጀመሪያው ምዕት ዓመት ጀምሮ የስሕተት ትምህርቶች የጥቃት ዒላማ ሆኖ የኖረ ክልል ነው። በ5ኛው መቶ የኬልቄዶኑ ጉባዔ ትክክለኛውን የሰብነቱን ትርጉም ቀምሮ ይፋ እስኪደረግ ድረስ የተለያዩ ቡድኖች በዚህ አስተምህሮ ዙሪያ ሲያውኩ ቆይተዋል። የክርስቶስን አንድ አካልና ሁለት ባህርይ ትርጉም የቀመረው የኬልቄዶን ጉባዔ በ451 ወይም በኛ አቆጣጠር በ443 ዓመተ ምሕረት የተደረገ ጉባዔ ነው። በንጉሥ መርቅያን ጠሪነት ከ600 የሚበልጡ ሊቃውንት የተቀመጡበት ይህ ጉባዔ ትልቅ ሸንጎ ነበር። የኬልቄዶኑ ጉባዔ ስለ ክርስቶስ አንድ አካልና ሁለት ባህርይ የቀመረው የትርጉሙ አጭር ቃል የሚከተለው ነው፤

*የክርስቶስ አካለ ትስባኤ (ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ) ሙሉ አምላክ፥ ፍጹም ሰው፥ ያለመደባለቅ (ያለመዋሃድ)፥ ያለውላጤ (ያለመለወጥ)፥ ያለመከፈል ወይም ያለመለየት ለዘላለም በአንድ አካል ይገኛሉ።*[2]

ከመጀመሪያው ምዕት ዓመት ጀምሮ እስከ ኬልቄዶኑ ጉባዔ ድረስ በክርስቶስ ማንነት ላይ የተነሱ ዋና ዋና የስሕተት ትምህርቶች ነበሩ። የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በየጊዜው ጉባዔ እየተቀመጡ ለስህተቶቹ ጠንካራ ምላሽ ሰጥተዋል።[3] ከላይ ከተጠቀሱት ኖስቲኮችና ዶሴቲስቶች ሌላ ኤብዮናውያን የሚባሉት ኢየሱስ የማርያምና የዮሴፍ የተፈጥሮ ልጅ ብቻ ነው ይሉ ነበር። በኒቅያ ጉባዔ የተወገዙት አርዮሳውያንም ኢየሱስ ፍጡር እንጂ ዘላለማዊና አምላክ አይደለም ይሉ ነበር። ንስጥሮሳውያን ክርስቶስ ሁለት አካሎች እንዳሉት ሲያስተምሩ አውጣኪያውያን ደግሞ ሙሉ ሰውም ሙሉ አምላክም ሳይሆን የተዋሃደ አንድ ባህርይ ነው ይሉ ነበር። ይህኛው የተዋሕዶ አስተምህሮ ነው። 9እነዚህ ስህተቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉባዔ ጠርተው እስኪቀመጡባቸው ድረስ የጎሉና ችግርም የፈጠሩ መሆናቸውን መረዳት ያሻል።

በወልድ ማንነት ላይ ከነዚያ ጉባዔዎች በኋላም ክርክር መነሣቱ አልቆመም። ዛሬም በክርስቶስ አካል ላይ የቆዩና አዳዲስም የሚነሱ የተሳሳቱ ትምህርቶች አሉ። በዚህ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የተነሳው የይሆዋ ምስክሮች ትምህርት የአርዮስ የስሕተት ትምህርት ትንሳኤ መሆኑን ልብ ይሏል። በተዋሕዶ እምነት የሚታየውም በኬልቄዶን ጉባዔ የተወገዘው አስተምህሮ ነው። በኢትዮጵያ ተዋሕዶ እምነትም ውስጥ በወልድ ማንነት ላይ ሦስት ያህል የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። ተዋሕዶ የሚባለው አንደኛው የጸናው ቦሩ ሜዳ በዐፄ

---

[2] Ryrie, p. 247.

[3] Ibid., p. 253.

ዮሐንስ እና በንጉሥ ምኒልክ ፊት በተደረገው ክርክር አሸንፎ መሆኑ በታሪክ መዛግብት ተጽፎ ይገኛል። አስተምህሮተ ሥላሴን ከሚክዱ ሌሎች የዘመኑ ትምህርቶች ወልድ ብቻ ወይም ኢየሱስ ብቻ ብለው የተነሡም አሉ። እኒህ ወልድ ኢየሱስ አብም ነው መንፈስ ቅዱስም ነው የሚሉ ናቸው። ይህም በመሠረቱ ከቃሉ የወጣ ስሕተት ነው። ዮሐንስ በመልእክቱ ውስጥ የሰጠን የሐሰተኞች አንድ መለኪያ ከላይ እንዳየነው በኢየሱስ ማንነት ላይ የሚሰጠው አሻሚ ያልሆነ ትምህርት ነው።

# የይሁዳ መልእክት (መጽሐፉ በሙሉ)

1 የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ፥ በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ፥

2 ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ።

3 ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለመዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።

4 ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፥ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ።

5 ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብጽ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

6 መኖሪያቸውንም የተውትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።

7 እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።

8 እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉ።

9 የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር፥ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም።

10 እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥ አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ።

11 ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል።





12 እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ እንደ እድፍ ናቸው፥ እንደ እረኞች ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይጠብቃሉ፥ በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው ደመናዎች፥ ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ ከነሥራቸው የተነቀሉ በበጋ የደረቁ ዛፎች፥

13 የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል፥ ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው።

14፥15 ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ፥ እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመጸኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።

16 እነዚህ እንደ ምኞታቸው እየሄዱ የሚያንጎራጉሩና ስለ ዕድላቸው የሚያጉረመርሙ ናቸው፥ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ አፋቸው ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል።

17 እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ፥

18 እነርሱ፥ በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባቾች ይሆናሉ ብለዋችኋልና።

19 እነዚህ የሚለያዩ ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

20 እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥

21 ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።

22 አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፥

23 አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።

24 ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው

25 ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፥ አሜን።

ይህን አጭር መልእክት ማን እንደጻፈው በግልጽ ተጽፎአል። የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ ነው። በዚያን ዘመን የእገሌ ልጅ እንጂ የእገሌ ወንድም እምብዛም ያልተለመደ አጠራር ነው። ምናልባት ያዕቆብ በኢየሩሳሌምዋ ቤተ ክርስቲያን እጅግ የታወቀ ሰው በመሆኑ ይሆናል ይሁዳ ይህን ያለው። ምንም እንኳ ይሁዳም ሆነ ያዕቆብ ራሳቸውን የጌታ ወንድሞች ብለው ባይጠሩም ሌሎች ጸሐፊዎች እነርሱ እንዲህ መሆናቸውን ሳይጠቅሱ አላለፉም። ማቴ.13፥55፤ ዮሐ.7፥3-10፤ ሐዋ.1፥14፤ 1ቆሮ.9፥5፤ እንዲሁም

ገላ.1፥19 ተመልከቱ። እነዚህ ራሳቸውን እንደ ጌታ ወንድሞች ያለመጥቀሳቸው እንደ አዲስ ኪዳን ሊቃውንት አባባል ተሰሚነታቸው ካላቸው የተለየ ግንኙነት የተነሣ እንዳይሆን በማሰብ ነው ተብሎ ይገመታል። እንግዲህ ይህ ይሁዳ የጌታ ግማሽ ወንድም የሆነው ይሁዳ መሆኑንም አስተውለን እንለፍ። ይልቁንም ራሱን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ሳይሆን ባሪያ አድርጎ ነው ያቀረበው። በስነ ትርጓሜ መጻሕፍተ ቅዱሳት ምዕራፍ እንደምናየው ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መገኘቱ ይሁዳ ቢጽፈውም የጻፈው በአፊዎት መሆኑንና ዋናው ምንጭ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ እናያለን።

የይሁዳ መልእክት በቀደምት ጸሐፍት አባቶች ዘንድ የተጠቀሰ ቢሆንም አንዳንዶች ቁጥር 9 እና 14ን በመጥቀስ ከቀኖና ውጭ ያሉ ጽሑፎችን ወስዶአልና ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ሊቆጠር እንዳይገባው አስበው ነበር። ነገር ግን ጤናማ ከሆነ ዳኝነት አንጻር ከታየ ማንም ጸሐፊ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የሌለባቸውም ቢሆኑ እንኳ ታሪካዊ ታማኝነት ያላቸውን ጽሑፎች ለምሳሌነታቸውም ሆነ ለይዘታቸው ሊጠቀም መቻሉ ግልጽ ነው። እርሱ ተጠቀመባቸው ማለት ግን እነዚህ ጽሑፎች መለኮታዊ ምስክርነትን ወይም ተቀባይነትን አገኙ ማለት አይደለም። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ በሐዋ. 17፥28 ለአቴና ሰዎች ሲናገር የራሳቸውን ባለቅኔ ጠቅሶ ያለውን፥ ለቲቶ ሲጽፍ ደግሞ በ1፥12 ላይ የቀርጤስ ሰዎች ነቢይ የሆነ ሰው የተናገረውን እንደጠቀሰ ማስተዋል በቂ ነው። ይሁዳም የጠቀሳቸው እነዚህ የአጸቅሪፋ ጽሑፎች በእርሱ መጠቀሳቸው ቀኖናዊ አያደርጋቸውም።

የይሁዳ መልእክት መቼ ስለመጻፉ ከመልእክቱ ከራሱ የምና ገኛቸው ውስጣዊ ማስረጃዎች አሉ። እኒህም ሁለት ፍንጮች ይሁዳ የጌታ ወንድም ከሆነ የሚኖርበትን ዕድሜ መገመትና በተጨማሪም መልእክቱ ስለሚዋጋቸው የስሕተት ትምህርቶች ሁኔታ ማጤኑ ና ቸው። የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በቁጥር 17-18 ላይ መልእክቱ የተጻፈላቸው ተቀባዮች የሐዋርያትን ትምህርት የሰሙ ያስመስላቸዋልና ጊዜው ያልራቀ መሆኑን ያመለክታል። የስሕተት አስተማሪዎችንና ትምህርቶችን መጋፈጥን በተመለከተ ደግሞ የይሁዳ መልእክት እንደ ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት የሚፋለመው ቆይተው የተነሱትንና በሁለተኛው ምዕት ዓመት የጎኑትን የስሕተት ትምህርቶች ሳይሆን በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን የዕድገት ዓመታት የተነሱትን ስህተቶች ነው። በዚህ አጭር መልእክት የተጻፉትን ስህተቶች በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ዘመናት ችግሮች ጋር ማስተያየቱ ምላሽ ሊሰጠን ይችላል። ሐዋ. 20፥29-30፤ ሮሜ. 6፥1፤ 1ቆሮ. 5፥1-11፤ 2ቆሮ. 12፥21፤ ገላ. 5፥13፤ ኤፌ. 5፥3-17፤ እና 1ተሰ. 4፥6 ይመልከቱ። ስለዚህ የተጻፈበት ዘመን ምናልባት ከ58 እስከ 72 ዓመተ ምሕረት ባለው





ጊዜ ነው። ይህ ግምት ብቻ እንጂ ከመልእክቱ ውስጥ የምናገኘው ውስጣዊ ማስረጃ የለም። የይሁዳ መልእክትና 2ጴጥ. 2 በጣም ተቀራራቢ ናቸው። በአሳብ ብቻ ሳይሆን የተጠቀሙባቸው ምሳሌዎችና ቃላት ጭምር ሳይቀሩ በብዙው ተመሳሳይነት አላቸው።

የይሁዳ መጽሐፍ አከፋፈል እንደሚከተለው ነው፤

- የሠላምታ ቃል፥ 1-2፤
- የተጻፈበት ምክንያት፥ 3-4፤
  - የመልእክቱ መለወጥ፥ 3፤
  - የለውጡ ምክንያት፥ 4፤
- ስለሐሰተኛ አስተማሪዎች ማስጠንቀቂያ፥ 5-16፤
  - የከሃዲዎች ፍርድ ከታሪክ ምሳሌነት፥ 5-7፤
    - ያላመኑ እስራኤል፥ 5፤
    - የወደቁ መላእክት፥ 6፤
    - ሰዶምና ገሞራ፥ 7፤
  - በዘመኑ የነበሩ ከሃድያን መልክ፥ 8-16፤
    - በቃል ተሳዳቢነታቸው፥ 8-10፤
    - ባህርያቸውና ተምሳሌያት፥ 11-13፤
    - የፍርዳቸው ትንቢት፥ 14-16፤
- ለአማኞች የተሰጠ ምክር፥ 17-23፤
- ማጠቃለያ የቡራኬ ቃል፥ 24-25፤

*ቁ፥ 1-2።* ይሁዳ በዘመኑ የዳብዳቤ አጻጻፍ ስልት የራሱን ማንነት ከጻፈ በኋላ ተቀባዮቹን ይጠቅሳል። የይሁዳ መልእክት በአንድ አጥቢያ ለነበሩ ክርስቲያኖች የተጻፈ አይደለም። *በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ* ሲል አማኞችን ሁሉ የጠቀለለ ነውና በዚህም ከጠቅላላ መልእክቶች ይመደባል። ተቀባዮቹን ሲጠቅስ 'ወዳጆች ሆይ' ብሎ በሰፊው ነው የሚጠራው፤ ቁጥር 3፤ 17 እና 20። በአሳቡ ከሁለተኛ ጴጥሮስ ጋር በጣም ይመሳሰላል። ተቀባዮቹ እንዲህ ሰፊ ከሆኑ ይሁዳ መልእክቱን እንዲጽፍ ያነሣሣው ችግር በዚያው ዘመን ያንኑ ያህል መስፋቱንም ያመለክታል። መጠራት የሚለው

አሳብ አማኞችን ሁሉ የጠቀለለ ቃል ነው። በአዲስ ኪዳን እንደምናገኘው ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ራሱ መጠራት ከሚል ግስ ጋር የተሠራ ነው። ክርስቶስን የተቀበሉ አማኞች በእግዚአብሔር ስለ መወደዳቸውና በክርስቶስ ስለመጠበቃቸው አዲስ ኪዳን በሰፊው ያስተምራል። እግዚአብሔር ዓለሙን የወደደው አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ነው። አንድያ ልጁን ሰጥቶ የተቤዣቸውን ደግሞ አብዝቶ እንደሚወድ ጥርጥር የለውም። ቃሉም ይህን አብዝቶ ያስተምራል። ከዚህ ፍቅርም ምንም ነገር ሊለየን አይችልም፤ ሮሜ. 8፥39። ይሁዳ የመልእክቱን ተቀባዮች በአብ ከመወደዳቸው ሌላ በራሱ በአብ ለኢየሱስ ክርስቶስ መጠበቃቸውንም ይናገራል። የእግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ጠባቂነት አሁንም በስፋት በቃሉ የሚገኝ ትምህርት ነው። ኢየሱስ ራሱም ስለጠባቂነቱ ሲያስተምር ራሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ በሚሰጥ እረኛ መስሎአል። ከእጁም ማንም ሊነጥቀን አይችልም። ይህ የጥበቃ አሳብ እንደገና በመልእክቱ መጨረሻ ባለው ቡራኬ ላይ ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ ለሚችለው ተብሎ ተጠቅሶአል። በቁጥር 2 ላይ ሦስት የሰላምታውን መልካም ምኞቶች ይገልጥላቸዋል፤ ምሕረት፥ ሰላም፥ ፍቅር እንዲበዙላቸው ይመኛል። እነዚህን ነገሮች እንደ አዲስ እንዲያገኙ አይደለም የሚመኘው። በእግዚአብሔር የተወደዱና ለክርስቶስ የተጠበቁ አማኞች ናቸውና እነዚህ ነገሮች አሉአቸው፤ ግን እንዲበዛላቸው ይመኛል።

ቁ፥ 3-4። ይሁዳ መልእክቱን ሊጽፍ የፈለገው ስለ ደህንነት በማስተማር ነበር። ምናልባት ልክ በሮሜ መልእክት እንደምናገኘው ያለ አጠቃላይ የሰውን ኃጢአት፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር፥ የክርስቶስን ቤዛነት፥ በእርሱም ስለሚገኘው ሕይወትና የዚህ ሕይወት ዕድገት ሊጽፍ ሳይዘጋጅ አልቀረም። ነገር ግን በፈንታው የስሕተት አስተማሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው የእግዚአብሔርን ጸጋ በሴሰኝነት በመለወጥ አማኞችን ከእውነት ፈቀቅ ማድረጋቸውን በማስተዋል የማስጠንቀቂያ መልእክት ሊጽፍ ወደደ። ይህን ለምን እንዳደረገ በቁጥር 3 እና 4 ላይ አመልክቶአል። የጻፈው ስለ ደኅንነት ሳይሆን ከስሕተት አስተማሪዎች ስለመጠበቅ ስለሆነ አሳቡ መለወጡና ቀድሞ ሊጽፍ ያሰበውን አለመጻፉ ይታያል። ምናልባት በዘመኑ በጣም አዋኪ የነበሩ ራሳቸውን እንደ ፍጹም መንፈሳውያንና የተለየ እውቀት እንደተቀበሉ የተለዩ ብሩካት አድርገው የሚቆጥሩ ግኖስቲክ ተብለው የሚጠሩ ቡድኖች በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ችግር ፈጥረው ነበርና ለዚያ ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል። ፩ኛ ዮሐንስም ይህን ችግር ለመቅረፍና ምላሽ ለመስጠት እንደተጻፈ ይታመናል። የይሁዳ አሳብ ተለውጦ እንዲህ እንዲሆንና ይህ እንዲጻፍ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ መሆኑ እውነት ነው፤ ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉት ሁሉ እንዲጻፉ ጸሐፊዎቹን የነዳ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነውና።





ሲጽፍ የመከራቸው ዐቢይ ምክር ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለተሰጠ ሃይማኖት እንዲጋደሉ ነው። ሃይማኖት የተባለው እምነት ነው። መልእክቱ አስቀድሞ በተጻፈበት ቋንቋ እምነትም ሃይማኖትም ተመሳሳይ ቃል አላቸው። ቃሉን እንደገና በቁጥር 20 ላይ ይደግመዋል። ይህ ሃይማኖት ወይም እምነት አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠ እምነት ነው። ያም እምነት በቃሉ ላይ በተገለጠው ጠቅላላ እውነት ላይ የተመሠረተ የደኅንነት መንገድ ነው። ፈጽሞ ሲል ለአንዴና ለመጨረሻ መሰጠቱን የሚያሳይ አባባል ነው። ተደጋግሞ የሚሰጥ፥ ደጋግሞም የሚቀበሉት አይደለም። ለሁሌም አንዴ የተሰጠ ነው። ደኅንነት የሚደጋገም ልምምድ አይደለም። ክርስቶስን ብዙ ጊዜ አንቀበለውም። ከደኅንነት በኋላ ደኅንነትን ሙሉ የሚያደርግ ምንም ነገር መጨመር አይቻልም። ደኅንነታችን ክርስቶስን ስንቀበል አንዴ ሙሉ ነውና።

ይህ አንዴ ፈጽሞ የተሰጠ እምነት ግን የሚጋደሉለት እምነት ነው። ገድል ነው። መጋደል የሚለው ቃል በመጀመሪያው ቋንቋ ለአንድ ነገር መታገል የሚል ትርጓሜን የያዘ ነው። እዚህ የተጠቀሰው የሚታገሉለት ነገር የተሰጠው ሃይማኖት ነው። ይህ ማለት ከዳንን በኋላ የራሳችንን ደኅንነት ፈጻሚዎቹ እኛ ነን፤ እግዚአብሔር አንዴ አድኖናልና ከዚያ በኋላ አይመለከተውም ማለት አይደለም። የደኅንነታችን ራስም ፈጻሚም እርሱ ነው። ይህ ግን እኛ ማድረግ ካለብን ነገር ነፃ አያደርገንም። እግዚአብሔር ቃሉን ሰጥቶናል፤ ማንበቡና በትጋት ማጥናቱ የእኛ ድርሻ ነው። ጸጋን ሰጥቶናል፤ በመስካችን መሰማራቱና በትሕትና ማገልገሉ የእኛ ኃላፊነት ነው። እንዲሁም ይሁዳ በመልእክቱ ውስጥ እንደሚያስጠነቅቀው ስሕተትን ማስተዋልና ከዚያም መጠበቅ የምንጋደልበት አንድ መስክ ነው።

ቁጥር 4 ላይ ማስጠንቀቂያውን በግልጽ ጽፎአል። ወደ ውስጣቸው ሾልከው የገቡ ከሃዲዎች አሉ። እነዚህ ከሃዲዎች አስቀድሞም ለዚህ ፍርድ የተጻፉ ናቸው። ይህ እንዲህ መጻፋቸው ስለ ሐሰተኞች ስሕተትና ስለሚከተላቸው ፍርድ የተነገሩትን ክፍሎች መጥቀሱ ይሆናል። ይሁዳ እነዚህ ሰዎች ሾልከው እንዳይገቡ እያስጠነቀቀ አይደለም። ቀድሞውኑ ገብተዋል። አገባባቸው ደግሞ ሾልከው ነው። ቀዳዳ አግኝተው ነው። የስሕተት ትምህርቶች ወይም አስተማሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገቡት ሾልከው ነው። በግልጽ፥ በበር አይደለም። ይህ የማና ቸውም የስሕተት አሠራር ዓይነተኛ ባህርይ ነው።

እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ጸጋን በሴሰኝነት ይለውጣሉ። ይህ ለውጥ በጸጋ ውስጥ መገኘትን ለሴሰኝነት፥ ለብልግና፥ ለክፋት፥ ለኃጢአት ፈቃድ አድርጎ እንደመውሰድ ነው። አማኞች ከጸጋ በታች ስለሆኑ ኃጢአት ቢሠሩ የእግዚአብሔር ጸጋ የገነነ ስለሆነ ይህ ኃጢአት እንደማይቆጠርባቸው ወይም በቀላሉ ይቅርታ

ስለሚያገኙ የወደዱትን እንዲያደርጉ ለማስተማር ይሞክራሉ። ይህ ግን ከክርስትና መሠረታዊ ትምህርት የራቀ ነው። ጸጋ መብዛቱ እውነት ነው፤ ጳውሎስ በሮሜ 5 ይህንን የጸጋ ወይም የስጦታ መብዛት ይናገራል፤ ነገር ግን፥ ጸጋው በዛ ብለን በኃጢአት ጸንተን እንዳንኖር በሮሜ. 6፥1 ላይ፥ 'ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም' ይላል። ይሁዳም አማኞች ከእንዲህ ያሉ ሰዎች እንዲጠበቁና የእግዚአብሔርንም የማዳኑን ጸጋ ምንነት አውቀው እንዲቃወሙአቸው ሊያሳውቅ ወደደ። ጸጋውን በሴሰኝነት ስለለወጡ ኃጢአተኞች ይላቸዋል፤ አምላክ የለሾች ወይም ሕግ የለሾች ናቸው። ደግሞም ንጉሣችንንና ጌታችንን ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሚክዱ ከሐዲዎች ይላቸዋል። አስቀድሞ የተጠቀሰው ጸጋውን በሴሰኝነት መለወጣቸው ተግባራዊ ክህደት ነው። ይህኛው ክህደት ደግሞ እንቢተኝነታቸው እርሱንና ጌትነቱን፥ ንጉሥነቱንም ያለመቀበላቸው ነው። ጌትነቱ ምንም እኩያና ተመሳሳይ የሌለው ነው። ብቻውን ያለውን የሚለው ሐረግም ይህንኑ የሚያጎላ ነው። ግን እንዲህም የሆነውን ጌታ አውቀው ወደው ይክዱታል። ይህ እዚህ ክህደት የተባለው ቃል በዕብ. 11፥24 ካለው የሙሴ እንቢ ማለት ጋር የሚመሳሰል ስር አለው። ይህ ክህደት አውቆና አመዛዝኖ እንቢ ማለት ነው። ስለዚህ እነዚህ ሾልከው የገቡ ሰዎች ከውስጥም ከውጭም ከሐድያን ናቸው።

*ቁ፥ 5-7።* ቀጥሎ ከቁጥር 5 እስከ 16 ባለው ክፍል ይሁዳ ማስጠንቀቂያውን በማስፋፋት ከቀደመው ታሪክም እየጠቀሰ የሐሰተኞቹን አስተማሪዎች ባሕርይ እና ፍርድ ይዘረዝራል። በመጀመሪያው ክፍል፥ ከ5-7 ከታሪክ አስረጅነትና ምሳሌነት የፍርዳቸውን አይቀሬነት ያሳይ ዘንድ ይጀምራል። ለዚህም ሦስት ምሳሌዎችን ይወስዳል።

የመጀመሪያው በቁጥር 5 የሚገኘው ከግብጽ የወጣው ሕዝብ ነው። ይህንን ሲጠቅስ አንባቢዎቹ ወይም ተደራስያኑ ከሚያውቁት እውነት በመነሣት ነው። ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ሲል ይጀምራል። እስራኤል ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን መግባታቸው የሚያውቁት ታሪክ ነው። እንዲያስተውሉት የተፈለገውና ላሳስባችሁ እወዳለሁ ያለው ነጥብ ግን ቀጥሎ ያለው አሳብ ነው። ከግብጽ የወጡት ሁሉ የገቡ አልነበሩም። ሕዝቡን አድኖአል፤ ሁሉም ወጥተዋል፤ ነገር ግን የማያምኑት በኋላ ጠፍተዋል። በመንገድ ቀርተዋል እንጂ አልገቡም። ከግብጽ ሲወጡ ከ20 ዓመት በላይ የነበሩት ምራቅ የዋጡ ሰዎች ሁሉ፥ ያም ሁሉ ተአምርና የጸናችውን የጌታን እጅ ያዩ አዋቂዎች ሁሉ ባለማመን ወይም በክሕደት ምክንያት ወደ ተስፋይቱ ምድር አልገቡም። ከኢያሱና ከካሌብ በቀር 20 እና የምድረ በዳው 40 ተደምሮ ከ60 ዓመት ዕድሜ በላይ ከነበረው





የገባ ሰው አልነበረም። የተስፋዋን ምድር እንደሚያወርሳቸው እግዚአብሔርን አላመኑምና ባለማመናቸው ጠፉ።

በቁጥር 6 ላይ የሚገኘው ሁለተኛው ምሳሌ መላእክት ናቸው። እዚህ የተጠቀሰው የእነዚህ መላእክት ኃጢአት በሁለት ሐረግ የተጠቀሰ አንድ ኃጢአት ይመስላል። ይህንኑ አሳብ በ2ጴጥ. 2፥4 እንደምናገኘው ኃጢአት ያደረጉ መሆናቸው ተጽፎአል። የኃጢአታቸው ምንነት አልተጻፈም ይሁዳ፥ 'መኖሪያቸውንም የተውትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን' ይለዋል። የተሰጣቸውን ሥልጣን፥ አለቅነት፥ ወይም ኃላፊነት ያልጠበቁ፥ መኖሪያቸውን ወይም ስፍራቸውን የተው ናቸው። መላእክትም እንደ ሰው ሁሉ ኃይለ ፈቃድ አላቸውና በፈቃዳቸው መገዛት ወይም እንቢ ማለት ይችላሉ። እንቢ ብለውም አጋንንት ሆነው የሰይጣን ተከታዮች የሆኑ ናቸው። ከዚህ እንደምንረዳው እነዚህ የወደቁ መላእክት ኃላፊነት ወይም ሥልጣን ነበራቸው፤ ደግሞም የተመደቡበት ስፍራ ወይም መኖሪያም ነበራቸው። ሁለቱንም የተውና ባለመታዘዝ ዋናውን አጥፊ መልአክ ሰይጣንን የተከተሉ ሆኑ። አለቅነታቸውን ጥለውና መኖሪያቸውን ትተው ዝም አልተባሉም፤ ቅጣትን ተቀብለዋል። ቅጣታቸውም በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ መጠበቅ ሆነ። እነዚህ ያልታዘዙ መላእክት እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ፥ ማለትም፥ የመጨረሻው የፍርድ ቀን ድረስ ከጨለማ በታች ታስረው እንዲቆዩ ተደርገዋል። ይህን ያደረገው ጌታ ነው። ቀደም ሲል ባየነው ክፍልም ያላመኑትን ያጠፋቸውም እርሱው ነው።

ሦስተኛው ምሳሌ በቁጥር 7 ይገኛል። እዚህ የተጠቀሱት ደግሞ የሰዶምና ገሞራ እንዲሁም በዙሪያቸው የነበሩ ከተሞች ናቸው። የእነዚህ ኃጢአት ደግሞ ዝሙትን ማድረግና ሌላ ሥጋን መከተል ነው። በጥቅሱ መግቢያ ላይ ያለው 'እንዲሁም እንደ እነርሱ' የሚለው ሐረግ ከመላእክቱ ጋር የሚያያዝ አሳብ ሆኖ፥ ነገር ግን፥ ቅጣትና ምሳሌነቱን ለማሳየት ነው እንጂ መላእክቱና እነሰዶም ባደረጉት ኃጢአት መመሳሰላቸውን ለማሳየት አይደለም።

የሰዶምና ገሞራ ሰዎች ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ፤ ዘፍ. 13፥13። ኃጢአታቸው እጅግ ከብዳ ነበር፤ 18፥20። ከሎጥና ቤቱ በቀር ሌሎች ጻድቃን በእነርሱ መካከል አልተገኙም። የከተሞቹ ጥፋት በዘፍ. 19 ተጽፎአል። በዚህ ክፍል ሌላ ሥጋን መከተል የተባለው በከተማቸው የተሰየመው ሰዶማዊነት፥ ወንድ ከወንድ፥ ሴትም ከሴት መተኛት ነው። በኃጢአታቸው መዘዝ ሁለቱ ከተሞችና በዙሪያቸው ያለ አገር ሁሉ ከሰማይ በዘነበ እሳትና ዲን ተቃጠሉ። ይሁዳ የዘላለም እሳት ያለው ይህን ከሰማይ የዘነበ እሳት ነው። ወደፊት የሚሆነው የኃጥአን ቅጣት መፈጸሚያም ይህ የማይጠፋ እሳት መሆኑን ቃሉ

ያስተምራል። እነዚህ ሦስት ጥፋቶችና ቅጣቶች እንደምሳሌ አድርጎ በመጠቀስ ይሁዳ ሾልከው ወደገቡት ስሕተተኞች ይዘልቃል።

*ቁ፥ 8-16*። ይህ ክፍል በአጠቃላይ በይሁዳ ዘመን የነበሩት እነዚያ የሐሰት አስተማሪዎች ምን እንደሚመስሉ ይናገራል። ቀደም ካለው ክፍል ጋር ለማያያዝ፥ 'እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ' በማለት ነው የሚቀጥለው። እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉ። እያለሙ ሲል ሕልም ወይም ራእይ እያዩ ማለት ነው። ምናልባት ይህንን ሕልማቸውን ወይም ተገለጠልን የሚሉትን ነገር የትምህርታቸውና የሥልጣናቸው ዋና መሠረት ሳያደርጉት አልቀሩም። እያለሙ ሦስት ነገሮችን ያደርጋሉ። በመጀመሪያ ሥጋቸውን ያረክሳሉ። ይህ ሰዶማዊ ግብራቸው ሳይሆን አይቀርም። ካልሆነም ማናቸውም ሥጋን ለርኩሰት የሰጠ ኃጢአት ነው። ሌላው ጌትነትን መጣል ነው። ይህ ጌትነት ስለ ጌታ በተለይ የሚናገር ሳይሆን በአጠቃላይ ሥልጣንን የሚያመለክት ቃል ነው። ጌታን እንደሚክዱት ቀደም ሲል በቁጥር 4 አይተናል፤ ይህ ሥልጣንን መጣል ነው። መጣል የሚለው ቃል ማርከስ እንደማለት ነው። መናቅና ማጣጣል ብቻ ሳይሆን ለሥልጣን አለመገዛትን ያሳያል። የጌትነት ወይም የሥልጣን ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው። እንደ እግዚአብሔር አሳብ ቢያስተዳድሩም ባያስተዳድሩም ለዓለምም ባለሥልጣኖችም እንኳ ሥልጣን የተሰጠው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እነዚህ ከሐዲዎች ጌትነትን ይጥላሉ፥ ለመንፈሳዊም ለዓለማዊም ሥልጣን አይገዙም። ሦስተኛው ነጥብ ሥልጣን ያላቸውን መሳደብ ነው። ይህ ጌትነትን ከመጣላቸው ወይም ካለመታዘዛቸው ያለፈ ድርጊት ነው።

ስለ ስድብ በሚናገርበት ጊዜ የሚሰጠው ምሳሌ አለ። ይህም በቁጥር 9 ላይ የተጠቀሰው ሊቀ መላእክት ሚካኤል ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ የሆነው ነገር ነው። ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ አይደለም። የይሁዳ መልእክት በቀደምት ጸሐፍት አባቶች ዘንድ የተጠቀሰ ቢሆንም አንዳንዶች ቁጥር 9 እና 14ን በመጥቀስ ከቀኖና ውጭ ያሉ ጽሑፎችን ወስዶአልና ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ሊቆጠር እንዳይገባው አስበው ነበር። ነገር ግን ጤናማ ከሆነ ዳኝነት አንጻር ከታየ ማንም ጸሐፊ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የሌለባቸውም ቢሆኑ እንኳ ታሪካዊ ተዓማኒነት ያላቸውን ጽሑፎች ለምሳሌነታቸውም ሆነ ለይዘታቸው ሊጠቀም መቻሉ ግልጽ ነው። እርሱ ተጠቀመባቸው ማለት ግን እነዚህ ጽሑፎች መለኮታዊ ምስክርነትን አገኙ ማለት አይደለም። ወይም በአዲስ ኪዳን ጸሐፊ ተጠቅሰዋልና ከቅዱሳት መጻሕፍት ተራ ሊቆጠሩ ይገባቸዋል ማለትም አይደለም። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ በሐዋ. 17፥28 ለአቴና ሰዎች ሲናገር የራሳቸውን ባለቅኔ ጠቅሶ ያለውን፥ ወይም ለቲቶ ሲጽፍ በ1፥12 ላይ የቀርጤስ ሰዎች ነቢይ የሆነ ሰው የተናገረውን እንደጠቀሰ ማስተዋሉ በቂ





ነው። ጸሐፊዎች እነዚህን የጠቀሱት ለትምህርት ወይም ለምሳሌያዊ ማብራሪያ ብቻ ነው። እዚህም የተጠቀሰው ክፍል *ዕርገተ ሙሴ (Assumption of Moses)* በሚባል የአጶቅሪፋ ጽሑፍ የሚገኝ ነው። አንዳንዶች ይህን ከሌላ ጽሑፍ የመወሰድን አሳብ አንሥተው ብዙ ውስብስብ ውስጥ ይገቡና ይሁዳ ሊል የፈለገውን ነገር ፈጽሞ ይዘነጉታል። ይህን የጠቀሰው ሥልጣንን ስለማክበር ነው። 'የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር፥ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም' ይላል። ሰይጣን ርኩስ መልአክ ነው፤ ሚካኤል ደግሞ ቅዱስ መልአክ ነው፥ ደግሞም የመላእክት አለቃ ነው። ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይጻፍና ባናውቀውም የሙሴ ሥጋ ጉዳይ መሆኑን እናውቃለን። ሙሴ የእግዚአብሔር ሰው ነውና ጉዳዩ ከዲያብሎስ ይልቅ ለሚካኤል የቀረበ ነው። እንዲህም ሁሉ ሆኖ እንኳ ሚካኤል በዲያብሎስ ላይ የስድብን ፍርድ ሊናገር አልደፈረም። ይህንን ነው ይሁዳ ከእነዚህ ጋር የሚያነጻጽረው። 2ጴጥ. 2፥11 ተመሳሳይ አሳብ ይናገራል።

እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥ አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ። ቁ፥ 10። ይህ ጥቅስ ሁለት ነገሮችን ይነግረናል የመጀመሪያው ተሳዳቢነታቸው ነው። ይህ አሳብ ቀደም ሲል የተጠቀሰና እዚህ የተደገመ ብቻ አይደለም፤ ቀደም ሲል በቁጥር 8 ላይ የተጠቀሰው ሥልጣን ያላቸውን መሳደባቸው ነው። ይህ እዚህ የተጻፈው ደግሞ የማያውቁትን ሁሉ መሳደባቸው ነው። ተሳዳቢዎች ብቻ ሳይሆኑ ስለዚያ ስለሚሳደቡት ነገር እውቀት የላቸውም። መሳደባቸው ሳያንስ የሚሳደቡት ስለማያውቁት ነገር ነው። ይህ ጥቅስ የሚነግረን ሁለተኛ ነገር እነዚህ ሰዎች የሚያውቁትን እውቀት የሚያገኙት እንኳ በማስተዋል ሳይሆን ልክ እንሰሳት በፍጥረታቸው ወይም በተፈጥሮአቸው በደመ ነፍስ እንደሚያገኙት ባለ ሁኔታ መሆኑን ነው። በዚህ ጎዶሎ እውቀታቸው ይጠፋሉ። ይህ ይጠፋሉ የሚለው ቃል ማርከስን፥ ማበላሸትን፥ ማክፋትን፥ ወደ ስሕተት መምራትን የሚያመለክት ቃል ነው። ራሳቸውንም ሌሎችንም ወደ ከፋ ጥፋት ውስጥ መምራትና መክተታቸውን ያሳያል። 2ጴጥ. 2፥12 ከዚህ ጋር ተመሳሳይ አሳብ ይናገራል።

ይሁዳ ከቁጥር 11 እስከ 13 ባሉት ጥቅሶች ውስጥ የነዚህን ሰዎች ባህርያት ይጠቅሳል። በቁጥር 11 ላይ፥ 'ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል' ይላል። በወዮታ ይጀምርና ከሦስት የብሉይ ኪዳን ሰዎች ጋር ያመሳስላቸዋል። ወዮታው ፍርድና ቅጣታቸው የማይቀር መሆኑን አረጋጋጭ ነው። የመጀመሪያው ምሳሌ በቃየን መንገድ መሄድ ነው። የቃየን

መንገድ ከታሪኩ እንደሚገኘው የንዴትና የጥላቻ፥ የበቀልና የነፍስ ማጥፋት መንገድ ነው። በዘፍ. 4 አቤል ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ማቅረቡ፥ በዕብራውያን መልእክት ደግሞ የበለጠ መስዋዕት በእምነት ማቅረቡ ተጽፎአል። ቃየል ወንድሙን የገደለው በዚህ የወንድሙ ንጹሕ አምልኮ ተቀባይነት ማግኘት ቀንቶ ነው። በይሁዳ የተጻፉት ከሐዲዎችም የእግዚአብሔር ሰዎች ንጹሕ አምልኮ አበሳጭቶአቸው በቁጣና በጥላቻ መንገድ የሚሄዱ ይመስላል።

ሁለተኛው ምሳሌ በለዓም ነው። 2ጴጥ. 2፥15-16 ላይም ጴጥሮስ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት ሲጽፍ ይህንኑ ሰው ጠቅሶ አመሳስሎአቸዋል። የበለዓም ታሪክ በዘኁ. 22-25 እና 31፥15-18 በሰፊው ተጽፎአል። እንዲሁም አሳች ትምህርቱ በአዲስ ኪዳንም በ2ጴጥ. 2፥15-16 እና በራእ. 2፥14 ላይ ተጠቅሶአል። ይሁዳ የጠቀሰው የሐሰተኛ አስተማሪዎችና ነቢያት ጥፋት ስለደመወዝ በዚህ ሰው በበለዓም ስሕተት መጥፋታቸው ነው። በለዓም በገንዘብ ፍቅር የተጠመደ፥ ገንዘብ ተቀብሎ ለመርገም ብዙ መቶ ኪሎ ሜትር ቆርጦ የመጣ ሰው ነው። ሌላው የዚህ ሰው ስሕተት እስራኤልን ወደ ምንዝርና መምራቱ ነው። እርግማኑ ወደ በረከት ሲለወጥ አፍሮ ወደ አገሩ አልተመለሰም፤ እዚያው ቀርቶ ሲያስት ኖሮ እዚያው ነው ከምድያማውያን ጋር የተገደለው፤ ዘኁ. 31፥8፤ 31፥16፤ ኢያ. 13፥22፤ ነህ. 13፥2። ይሁዳ የሚጠቅሳቸው ሐሰተኞች በሁለቱም፥ ማለትም፥ በፍቅረ ንዋይም በሴሰኝነትና ወደ ሴሰኝነት በመምራትም ከበለዓም ጋር ይመሳሰላሉ።

ሦስተኛው ምሳሌ ቆሬ ነው። 'በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል' ይላል። ታሪኩ በዘኁ. 16 ይገኛል። ከቆሬ ጋር አብረው የተጠቀሱ ሌሎች ሦስት፥ ደግሞም 250፥ ደግሞም ከእስራኤል ጉባኤ የተመረጡና ዝነኞች የነበሩ ሌሎችም ሰዎች አብረው መሆናቸው ተጽፎአል። በይሁዳ ከሌሎቹ ይልቅ ቆሬ መጠቀሱ የመሪነቱን ሚና የተጫወተ ያስመስለዋል። ደግሞም በዘኁ. 26፥ 9-10 እንደገና መጠቀሱና ከሌዊ ወገንም መሆኑ እንደ ቡድኑ መሪ ያስመስለዋል። የቆሬና የግብረ አበሮቹ ጥፋት የሙሴን ሹመት አለመቀበል ነው፤ መሠረቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሥልጣንን መቃወም ነው። ሐሰተኛ ነቢያትም ሥልጣን ያላቸውን እንደሚሳደቡ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ሙሴ በሕዝቡ ላይ መንፈሳዊ መሪ ብቻ ሳይሆን ሊስተዳደራዊ አለቃም እንደነበር ይታወቃል። ይሁዳ ይህን የጠቀሰው በተለይ መንፈሳዊ ሥልጣንን ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መቃወማቸውን ለማመልከት ይመስላል። ዋና የጥቃት ትኩረታቸው ቤተ ክርስቲያን ናትና።

ይሁዳ እንዲህ ካመሳሰላቸው በኋላ በቁጥር 12 እና 13 በመቀጠል ባህርያቸውን ይዘረዝራል። በዚህ ክፍል በጣም ገላጭና





ስዕላዊ የሆኑ ቃላትና ተምሳሌቶች ይጠቀማል። በመጀመሪያ በእድፍ ይመስላቸዋል። 'እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ እንደ እድፍ ናቸው' ይላል። 2ጴጥ. 2፥13 በፍቅር ግብዣ እንደሚዘፍኑ ይላል። የፍቅር ግብዣ የመጀመሪያዎቹ አማኞች በአምልኮአቸው ጊዜ የጌታን ራት ካሰቡ በኋላ የሚያደርጉት የምግብ ግብዣ ነው። እነዚህ ሰዎች በዚህ የተቀደሰ ጉባኤም እንኳ እስከሚገኙና የራሳቸውን አሳፋሪ ድርጊት እስከሚፈጽሙ ሾልከው ገብተዋል። የእድፍ እድፍነት ጎልቶ የሚታየው ያለቦታው በንጹሕ ስፍራ ሲገኝ ነው። ይሁዳ እነዚህን በዚህ ቅዱስ ጉባኤ እንደተገኙ እድፍ ይመስላቸዋል።

ሌላው የተመሰሉት ራሱን በሚጠብቅ እረኛ ነው። 'እንደ እረኞች ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይጠብቃሉ' ይላል። ልክ በሕዝ. 34 እንደተጻፉት እረኞች ወይም ጌታ በዮሐ. 10 እንዳስተማረው እንደ ሞያተኛው እረኛ ማለት ነው። እውነተኛ እረኛ ነፍሱን ወይም ራሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል እንጂ ራሱን አይጠብቅም። ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ግን ከሁሉ በፊት ራሳቸውን ነው የሚመስጉት፥ የሚመግቡትና የሚያጠግቡት። የሌላው ሳይሆን የራሳቸው እረኞች፥ የራሳቸው መጋቢዎች ናቸው።

ሦስተኛ ውኃ በሌለባቸው ደመናዎች ይመስላቸዋል። 'በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው ደመናዎች' ይላቸዋል። ደመና የዝናም ምንጭ ነው። ደመና ከኖረ የዝናም፥ የእርጥበት፥ የመረስረስ፥ የመርካት ተስፋ አለ ማለት ነው። ይህ እንዲሆን ግን ደመናው እውነተኛ ደመና፥ ዝናም ያዘለ ደመና መሆን አለበት። ሐሰተኛ ነቢያት ግን ተስፋ የሚመስል ነገር አላቸው፤ የሚያረካ የሚያረሰርስ የሚመስል መልክ አላቸው፤ ግን በቃ መልክ ብቻ ነው። እንደተመሰሉበት ደመና ናቸው፤ ግን ደረቅ፥ ውኃ የሌለባቸው፥ በነፋስ የሚነዱ ደመናዎች ናቸው። የሚሰጡ ይመስላሉ፤ ግን የሚሰጡ የሚመስሉት ነገር በእጃቸው የለም። የተወሰዱ የሚለው ቃልም በስፍራቸው የሌሉ፥ ስፍራም የሌላቸው የሚሰኝ ነው። ጴጥሮስ ውኃ የሌለባቸው ምንጮችና በዐውሎ ነፋስም የተነዱ ደመናዎች ይላቸዋል፤ 2ጴጥ. 2፥17።

አራተኛ በደረቅ ዛፍ ይመስላቸዋል። 'ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ ከነሥራቸው የተነቀሉ በበጋ የደረቁ ዛፎች' ይላቸዋል። ይህ እዚህ በጋ የተባለው በዚያ አካባቢ ወቅት ዛፎች ፍሬ የሚያፈሩበት ጊዜ ነው። በበጋ ዛፎች ሁሉ ፍሬያማ ይሆናሉ። በዚህ ጊዜ ፍሬቢስ መሆን እውነትም ፍሬቢስ መሆን ነው። በፍሬ ጊዜ ፍሬቢስ መሆን ብቻ አይደለም፤ በዚህ በፍሬ ጊዜ ከነሥራቸው የተነቀሉ ናቸው። ስለዚህ ሁለት ጊዜ የሞቱ ናቸው። ከላይ ፍሬ የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ ከሥርም የተነቀሉ ስር

የሌላቸው ናቸው። የፍሬ ብቻ ሳይሆን የመኖር፥ የሕይወት ተስፋም የላቸውም።

አምስተኛ *የገዛ ነውሩን ከውስጡ በሚያወጣ በጨካኝ የባሕር ማዕበል* ይመስላቸዋል። 'የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል' ይላቸዋል። እየደፈቁ የሚለው የሚደፍቁ ቢባል ሐረጉ ግልጽ ይሆንልናል። አሳቡም እንዲያ ነውና። ጨካኝ ሲል ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ታላቅ፥ ጠንካራ ለማለት ነው። ልክ ማዕበል ከባሕሩ ውስጥ ጉድፍ እንደሚያወጣ እነዚህም ከውስጣቸው የሚያወጡት ወይም የሚደፍቁት የገዛ ነውራቸውን ወይም አስነዋሪ ሥራቸውን ነው።

ስድስተኛ *በሚንከራተቱ ከዋክብት* ተመስለዋል። በቁጥር 13 ላይ ይሁዳ፥ 'ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው' ይላል። የሚንከራተቱ ሲል ከምሕዋር ወይም ከሚዞሩበት ጎዳና ለቅቀው እንደወጡ ፕላኔቶች እንደማለት ነው። ከዋክብትም ፕላኔቶችም በራሳቸው እንዝርት እየሾሩ ሌላ ትልቅ አካልን የሚዞሩበት የምሕዋር ዐውድ አላቸው። ጉዞአቸው በፈጣሪ ሥርዓት የተደረገለት ነው፤ ያንንም ይከተላሉ። እነዚህ ግን በምሕዋራቸው ሳይሆን ያለምሕዋራቸው እንደሚነጉዱ፥ እንደሚንከራተቱ ከዋክብት ተመስለዋል። የሚንከራተቱ የሚለው ቃል ለሌላ ሲውል ማረፊያ፥ ማደሪያ የሌላዘው ዘላኖች እንደማለትም ነው። አካሄዳቸው ሁሉ ያለመስመር፥ ያለሥርዓት ነው። ከዚህም ሌላ ፍጻሜያቸውን ሊያሳይ የፈለገ ይመስላል ይሁዳ። እነዚህ ሰዎች አሁን እንደሚንከራተቱ ከዋክብት ብቻ ሳይሆኑ ፍጻሜያቸውም ድቅድቅ ጨለማ ነው። 2ጴጥ. 2፥17 ላይ ይህም ተጠቅሶአል። ድቅድቅ ጨለማ ከእግዚአብሔር ተለይተው ለዘላለም የሚቀጡበትን ስፍራ የሚያሳይ ነው።

ቁጥር 14 እና 15 የሄኖክን ትንቢት ይጠቅሳል። ቀደም ሲል በቁጥር 9 ከቀኖና ውጭ ያለ ጽሑፍ መጠቀሱን አይተናል። እዚህም የተጠቀሰው ሄኖክ የተናገረው ነገር የሄኖክ ታሪክ በሚገኝበት በዘፍ. 5 አይገኝም። ነገር ግን *መጽሐፈ ሄኖክ* በሚባል የአጸቅሪፋ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። ይሁዳ የጠቀሳቸው እነዚህ የአጸቅሪፋ ጽሑፎች በእርሱ መጠቀሳቸው እነዚህን መጻሕፍት ቀኖናዊ እንደማያደርጋቸው ቀደም ብለን አይተናልና መድገም አስፈላጊ አይደለም። ይህ መጽሐፍ በሄኖክ እንደተጻፈ ነው መጽሐፉን የሚቀበሉት ክፍሎች የሚናገሩት። ይሁን እንጂ እስከ 100 ዓመተ ዓለም ድረስ መኖሩ አይታወቅም ነበር፤ ወይም ያልነበረ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመናት የታወቀ ጽሑፍ ነበረ። በቀኖና መጻሕፍተ ቅዱሳት ውስጥ ያልገባ መሆኑ በውስጡ እውነት የለም ማለት አይደለም። ይሁዳ በውስጡ ካሉት ነጥቦች አንዱን እውነት ነጥሎ ወስዶ ነው እዚህ





መልእክቱን አጠንክሮ ለማስተላለፍ የተጠቀመበት። ሄኖክ በዘፍ. 5 እንደሚገኘው ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ ሰው ነው። ሰባተኛነቱን የጠቀሰው ያ ሄኖክ መሆኑን ለመንገር ነው እንጂ ሰባተኛ መሆኑ ምንም ሆኖ ወይም የተለየ ትርጉም ኖሮት አይደለም። የሄኖክ ትንቢት እንዲህ የሚል ነው፤ 'እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመጸኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ' ይላል። የትንቢቱ ዋና አሳብ ጌታ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር ሊፈርድና ሊወቅስ መጥቶአል የሚል ነው። መጥቶአል የሚለው የኃላፊ ቃል ቢሆንም ዳግመኛ ስለመምጣቱ የተነገረ ጠቅላላ ትንቢት ነው። አእላፋት ቅዱሳኑ መላእክቱ፥ ወይም ከመነጠቅ በኋላ ዳግም ሲመጣ አብረውት የሚመጡ ቅዱሳን ሰዎች፥ ወይም ሁለቱም ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ የተከማቸው ኃጢአት የሚለው ቃል መደጋገም የእነዚህን ሰዎች ባህርይ ያሳያል። እንዲህ መደጋገሙ ፍርዳቸውም በዚያው ልክ መሆኑን ለመግለጥ ይመስላል።

በቁጥር 16 ላይ እንደገና ባህርያቸው በተጨማሪ ይነገራል። 'እነዚህ እንደ ምኞታቸው እየሄዱ የሚያንጎራጉሩና ስለ ዕድላቸው የሚያጉረመርሙ ናቸው፥ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ አፋቸው ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል' ይላል። በዚህ ጥቅስ የተነገረው የመጀመሪያው ነጥብ እነዚህ ሰዎች *እንደ ምኞታቸው መሄዳቸው ነው*። እንደሚመኙት፥ እንደሚፈልጉት ይመላለሳሉ። ዳርና ድንበር፥ ሕግና ደንብ፥ ሥርዓትና መስመር የላቸውም። የተመኙትን ነገር ለማድረግ ምንም ተዐቅቦ የሚያደርግባቸውን ነገር አይሹም። በአንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎች ዘንድ እንደሚታየው እንዲህ ያሉት ሰዎች አንዳንዴ ለምኞታቸው መድረሻ የእግዚአብሔርን ጸጋና ነፃ አውጪነትም ይጠቅሱ ይሆናል።

ሁለተኛው ነጥብ *ማንጎራጎርና ማጉረምረም ነው*። የሚያንጎራጉሩትና የሚያጉረመርሙት እንደገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ነው። ማንጎራጎርና ማጉረምረም የሚቀራረቡ ግን የተለያዩ ቃላት ናቸው። ማንጎራጎር በሌላ ላይ የተቃጣ ክስ፥ ሌላው በሚያደርገው ነገር ስሕተትን በመፈለግ መናገር ሲሆን ማንጎራጎር ደግሞ በራስ አለመከናወን፥ አለመሳካት፥ አለመቃናት አለመርካት የተነሣ የሚደረግ እንጉርጉሮ ነው። እነዚህ ሰዎች ሁለቱንም ያደርጋሉ። በራሳቸው ኑሮ በሚያዩት ጎዶሎ ይረበሻሉ፤ በሕይወታቸው አይረኩም፤ ኑሮዩ በቃኝ ማለት ከኃጢአት እኩል ይመስላቸዋል፤ ደግሞም በሌላው ላይ በሚያዩት መልካም ይቀናሉ፤ አይደሰቱም።

ሦስተኛው ነጥብ *ታላቅ ቃል መናገር* ነው። በአማርኛው ጥቅስ አብሮ የተገመደ ቢሆንም በጥቅሱ ውስጥ ሁለት አሳቦች ይገኛሉ። አንዱ *ታላቅ ቃል* የተባለው ከልክ ያለፈ የትምክህትና የኩራትን ነገር የሚናገር ቃል ነው። ይህ ስለራሳቸው ያላቸው የተጋነነ ንግግር ነው። ሌላው በዚሁ ውስጥ ያለው አሳብ ለጥቅማቸው ሲሉ ወይም ሌሎችን መጠቀሚያ፥ ማትረፊያ ለማድረግ ሲሉ የሰዎችን ፊት እያዩ ወይም ለሰው እያደሉ ስለነዚያ ሰዎች የሚናገሩት የተጋነነ ንግግር ነው። እነዚህ በራሳቸው ትምክህት የሰከሩ ሰዎች ናቸው። ስለራሱ እያጋነኑ ሲናገሩለት የሚሞቀውን ሌላ ሰው ሲያገኙም ከመካብ አይመለሱም።

እነዚህ ሁሉ ከላይ ከቁጥር 5-16 ያየናቸው የተለያዩ ነጥቦች የሐሰተኛ አስተማሪዎችንና ነቢያትን ባህርያት የያዙ ጥቅሶች ና ቸው። ሾልከው ከገቡ ከሐሰተኞች እንዲጠነቀቁና እንዲጠበቁ ስለሰዎቹ እንዲህ ከዘረዘረ፥ ካብራራም በኋላ አሁን ወደ አማኞች ይዞራል። ከ17-23 ያለው ለአማኞች የተሰጠ ምክር ክፍል ነው።

ቁጥር 17-18 አስቀድሞ የተነገራቸውን ቃል ያሳስባል። 'እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ፥ እነርሱ፥ በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባቾች ይሆናሉ ብለዋችኋልና' ይላል። አስቀድሞ ጥንት በሄኖክ የተነገረውን ጠቀሰ። አሁን ደግሞ በቁጥር 17 ላይ በራሳቸው ዘመን የነበሩ የጌታ ሐዋርያት የተናገሩትን ያሳስባቸዋል። አስቀድሞም በኋላም ስለሐሰተኞች ነቢያትና አስተማሪዎች ትንቢት የተነገረ በመሆኑ ይሁዳ የሚጽፍላቸው አማኞች አስተዋዮች ከሆኑ ቀድመው መጠንቀቅ ይችላሉ። ስለዚህም በሐሰተኞች ድንገተኛ ወረራ ሊደርስባቸው አይችልም። እነዚህ ሐዋርያት የይሁዳን መልእክት ተቀባዮች መቼና እንዴት እንዳስጠነቀቁአቸው አናውቅም። ከጌታ ቀጥሎ የኖሩና ያገለገሉ ሐዋርያት የተናገሩአቸው ማስጠንቀቂያዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ አልፎ አልፎ ተጽፈው እናያለን። ለምሳሌ፥ ሐዋ. 20፥29፤ 1ጢሞ. 4፥12፥2-9፤ 6፥3-10፤ ቲቶ. 1፥10-13፤ 2ጴጥ. 2፤ 1ዮሐ. 2፥18-23፤ 4፥1-6፤ ወዘተ። እነዚህ የመልእክቱ ተቀባዮች እነዚህን ወይም እንዲህ ያሉትን ማስጠንቀቂያዎች የሰሙ ናቸው። ይሁዳ ይህን የሰሙትን ቀድሞ የተነገራቸውን ቃል ያሳስባቸዋል። ዛሬም ያው መንፈስ ስለሆነ በሥራ ላይ ያለው የቃሉ አገልጋዮች ማስተማርና ማስጠንቀቅ፥ ሰሚዎችም ማሰብና ማስተዋል አለባቸው።

ቁጥር 18 እነዚህ የክርስቶስ ሐዋርያት ስለሐሰተኞች የተና ገሩትን ይደግማል። 'እነርሱ፥ በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባቾች ይሆናሉ ብለዋችኋልና' ይላል። የመጨረሻው ዘመን ያኔም የመጨረሻው የተባለው አሁንም ያለንበት ከጌታ መምጣት በፊት ያለው ጊዜ ሁሉ ነው። ነገር ግን





ከእነርሱ ይልቅ እኛ ለመጨረሻው የቀረብን መሆናችንን ልብ ልንል ይገባል። ቀደም ሲል በኃጢአተኝነትና እንደገዛ ምኞታቸው የሚሄዱ መሆናቸውን አይተናል። እዚህም ደግሞ ይህንን ባህርያቸውን ከሐዋርያቱ ትምህርት ጋር አያይዞ ያቀርበዋል። በተጨማሪም ዘባቾች እንደሚሆኑ ይናገራል። ዘባች ማለት አፌያኝ፥ ቀላጅ፥ ቀላማጅ፥ ሌላውን መሳቂያ መሳለቂያ ሊያደርግ የሚያጣጥል ማለት ነው። እነዚህም እንደገዛ ምኞታቸው በኃጢአተኝነት በመሄድ እንዲህ የሚዘብቱ ናቸው። 2ጴጥ. 3፥3ም ተመሳሳይ ነገር ይጠቅሳል።

በቁጥር 19 ተጨማሪ ባህርያት ተጽፈዋል። ጥቅሱ፥ 'እነዚህ የሚለያዩ *ሥጋውያንም* የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው' ይላል። በመጀመሪያ የሚለያዩ መሆናቸውን ይናገራል። መለየት አንድነትን መናድ፥ ኅብረትን ማናጋትና መክፈል ነው። ይህ የማና ቸውን የስሕተት ትምህርቶችና የሐሰተኛ አስተማሪዎች ቋሚ ባህርይ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገቡና በምዕመናን መካከል አንዱ ከሌላው የሚለይበትን ነገር በመፍጠር ወይም በማቅረብ ስውር መቃቃርን፥ ብሎም ግልጽ መከፋፈልን ይፈጥሩና ከእነርሱ ጋር የሚያብረውን ቡድን ይወስዳሉ።

*ሥጋውያን* ሲል መንፈሳውያን ያልሆኑ በፍጥረታዊ አስተሳሰባቸው የሚመሩና የሚመላለሱ ለማለት ነው። መንፈሰቢስ ወይም መንፈሳዊነት አልባ የሆኑ እንደማለት ነው። መንፈስ የሌላቸው ሲልም የእግዚአብሔር መንፈስ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደሌለባቸው መናገሩ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሌላቸው እነዚህ ሰዎች ድነው የሳቱ ሳይሆኑ ከቶም ያልዳኑ ናቸው። በራሳቸው ግምት ራሳቸውን ከሌላ የተሻለ መንፈሳዊ አድርገው ቢቆጥሩና ቢመለከቱም እነዚህ የእግዚአብሔር መንፈስም መንፈሳዊ ዝንባሌም የሌላቸው ሰዎች ናቸው። በቁጥር 10 ላይ እንደተመለከትነው እነዚህ ሰዎች በፍጥረታዊ አእምሮአቸው እየተነዱ የሚጠፉ ሰዎች ናቸው።

በቁጥር 20 ላይ እንደገና 'እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ' ይላል። በቁጥር 17 ላይ የጀመረውን አሳብ እንደገና ማጠንከሩ ነው። በመካከልም በቁጥር 18-19 ስለ ሐሰተኞች በመናገሩ እንደገና በንጽጽር ወደእነርሱ መመለሱ ነው። በዚህ ደግሞ በመጀመሪያ 'ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ' ይላል። ይህ የተቀደሰ ሃይማኖት በቁጥር 3 ላይ አስቀድሞ የተጠቀሰው እንዲጋደሉለት የተነገራቸው ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠው እምነት ነው። ይህን ሃይማኖት በቁጥር 3 ላይ ጠቅለል አድርጎ ሲያቀርበው እዚህ ግን ተሳቢ ያደርገዋል። የእና ንተ ሃይማኖት ያሰኘዋል። ሃይማኖቱን ደግሞ የተቀደሰ ይለዋል። ይህ የተቀደሰ የሚለው አሳብ እስካሁን ሲዘረዝር ከቆየው የሐሰተኞች ባህርይ ፈጽሞ የራቀ ባህርይ ነው። እንዲያውም

ሃይማኖቱ መቀደሱን ለመግለጥ የተጠቀሰው አበላላጭ ቃል ነው፡ ቃሉ እጅግ በተቀደሰ የሚሰኝ ነው። ይህን ቃል የተጠቀመው ልዩነታቸውን ይበልጥ ለማሳየት ይመስላል። ይህ እጅግ የተቀደሰው የተቀባዮቹ እምነት ምን መሆኑ በመልእክቱ መግቢያ ላይ በእግዚአብሔር አብ ከመወደዳቸውና ለኢየሱስ ክርስቶስ ተጠብቀው ከመጠራታቸው አሳብ ይታያል። እነዚህ በክርስቶስ ያመኑ በደሙም የነጹ ቅዱሳን ናቸው። ይህ ነው እጅግ የተቀደሰ ሃይማኖት።

ይህ ሃይማኖት ወይም እምነት ራስን የሚያንጽ ነው። ለዚህ ነው በዚህ እምነት ራሳቸውን ለማነጽ እንዲተጉ ያለው። ማነጽ መገንባትና ማጠንከር ነው። ይህ እምነት ራስን ያንጻል፥ ያጠነክራል፥ ይገነባል። ይህ እንዲሆን ግን ትጋት ይጠይቃል። አምኖ ብቻ መወዘፍ አይገነባም። 'እየተጋችሁ' ይላቸዋል። ትጋት ጥረት ነው። ለመዳን ምንም ጥረት አንጠየቅም የተፈጸመውን ከመቀበል በቀር። ሆኖም እነጻና ግንባታ፥ ዕድገትና ጥንካሬ ግን ልፋት ይጠይቃል። ይህ የመታነጽ ትጋት ከስሕተት ትምህርትና አስተማሪዎች እንደሚጠብቅም ጥርጥር የለውም። ደግሞም፥ 'በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ' ይላል። ክርስቲያንን ለጸሎት የሚያነሣሣም፥ በጸሎት ጊዜው የሚያተጋም መንፈስ ቅዱስ ነው። ጳውሎስም ይህንኑ አሳብ በኤፌ. 6፥18 እና ሮሜ. 8፥26-27 ላይ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ ባነሣሣ ቁጥርም ባበረታ ልክም የመጸለይን አስፈላጊነት መረዳት ተገቢ ነው። ጸሎት ሥርዓት አይደለም። ጊዜና ቦታ አይወሰንለትም። በሁኔታዎችም አይገደብም። ጸሎት የግንኙነት መግለጫ ነው። ልባችን በናፈቀው ልክና ጊዜ ሁሉ ልንጸልይ፥ መንፈሱም ባነሳሳንና ባጎለበተን መጠን ልንጸልይ ይገባናል።

በቁጥር 21 ላይ፥ 'ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ' ይላል። ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደው፥ እኛም የምንጠባበቀው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረት ነው። አስቀድሞም ያዳነን በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ነው። እስካሁን ያኖረንም ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያስገባን ምሕረቱ ነው። ይህን ምሕረት ስንጠባበቅ ግን የምናደርገው የሚጠበቅብንም ኃላፊነት አለ። ያም በእግዚአብሔር ፍቅር ራስን መጠበቅ ነው። ከፍቅሩ የሚለየን ምንም እንደሌለና አስቀድሞ የወደደንም ገና ጠላቶቹ ሳለን መሆኑን ጳውሎስ ያስተምራል። በቡራኬው ክፍል ይሁዳ ሳንሰናከል ሊጠብቀን የሚቻለው ጌታ ብቻ መሆኑን ይና ገራል። እዚህ ግን በፍቅሩ ውስጥ ራሳችንን እንድንጠብቅ ያሳስባል። በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ራስን መጠበቅ ወይም ማቆየት ፈቃድን ይጠይቃል። ስለዚህ ነው ነገሩን የኛ ኃላፊነት ያደረገው።





ከላይ ከቁጥር 20 ጀምሮ ያየናቸው ጥቅሶችና ቀጥሎ ያሉትም 22-23 የስሕተት አስተማሪዎችን ወይም በስሕተት አስተማሪዎች ተጽዕኖ ስር ያሉትን እንዴት መቅረብ እንዳለብንም የሚናገሩ ጥቅሶች ናቸው። ራስን እያነጹ በጸሎት ከመትጋትና ምሕረቱን እየተጠባበቁ በፍቅሩ ራስን ከመጠበቅ ሌላ ተከራካሪዎችን እንዴት መቅረብ እንደሚገባን ይናገራል። ቁጥር 22፥ 'አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ' ይላል። ተከራካሪ የተሰኘው ቃል ተከራካሪም ተጠራጣሪም ሊሰኝ የሚችል ነው። ተከራካሪ ከሆኑ ለማሳት የሚከራከሩ ናቸው፤ ተጠራጣሪ ከሆኑም ያልተረዱና የሳቱ ናቸው። ውቀሱ የሚለው ግስ መልእክቱ መጀመሪያው በተጻፈበት ቋንቋ ምሕረትን አሳዩ እንደ ማለት ነው። መውቀስ ብዙውን ጊዜ ጥፋትም ማሳየት ሲሆን ይህ የይሁዳ ምክር ግን እነዚህ ሰዎች ተከራካሪዎችም ወይም ተጠራጣሪዎች ቢሆኑ እውነትን ያላወቁ ና ቸውና እውነትን ያወቁ ሰዎች በርኅራኄ ወደ እውነት መሳብ እንዳለባቸው ያሳያል።

ቁጥር 23፥ 'አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ' ይላል። እሳት የሚጠብቃቸውን ፍርድ የሚያሳይ ነው። አንዳንዶቹ ለዚህ ፍርድ አስቀድመው የተጻፉ መሆናቸውን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ከመካከላቸው ግን ወደ እውነት የሚመጡ መኖራቸውንም ይህ ክፍል ያሳያል። ከእሳት ነጥቆ ማዳን ከሚጠብቃቸው ፍርድ መመለስን መናገሩ ነው። ይህ መንጠቅ ትግልን፥ ወረራን፥ በጉልበት መውሰድን የሚያሳይ ቃል ስለሆነ ዋጋ የሚጠይቅ ነገር ያለበት ተጋድሎ ነው። በሥጋ የረከሰው ልብስ ርኩሰት መሥራትን የለመደ ሥጋቸውን ወይም ገላቸውን የነካው ልብስ ነው። እንኳን ሥራቸውን ሥጋቸውን የነካ ልብሳቸውንም እየተጸየፋችሁ፥ እየጠላችሁ እነርሱን ግን በፍርሃት ማሩ ነው የሚለው። ይህ የረከሰ ልብስ የኃጢአታቸውን መግነን የሚያሳይ ስዕላዊ ምሳሌም ነው። በዚህ ክፍል ከምሕረት ጋር የተደባለቀው ፍርሃት ራስን ከፈተናና በኃጢአታቸው ከመጠላለፍ የመጠበቅ ወይም ከላይ ከተመለከትነው የጌታን ምሕረት ከማግኘታችንና ከመጠባበቃችን ጋር የተያያዘ የውለታ፥ የአክብሮት ፍርሃት ሊሆን ይችላል።

ይሁዳ በመልእክቱ ውስጥ በአብዛኛው ሾልከው ስለገቡት የሐሰት አስተማሪዎች ይተነትናል። ቀጥሎም አማኞች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ያሳስባል። ወደ መጨረሻው ቡራኬ ሲተላለፍና መልእክቱን ሲደመድም ደግሞ አትኩረቱን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ ያደርጋል። ቁጥር 24 ላይ፥ 'ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው' ይላል። ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ችሎታ ይናገራል። ቅዱሳንን ከመሰናከል፥ ከመጠለፍ፥ ከመውደቅ

ሊጠብቅ የሚቻለው አምላክ እግዚአብሔር ነው። በተለይ የስሕተትን ትምህርትና አስተማሪዎች ለመቃወምና ለማስጠንቀቅ ተጻፈ መልእክት ውስጥ እንዲያ ያለ ተስፋን ማስፈር የአማኞችን ልብ በችግሮች ብዛት እንዳይርድ የሚደግፍ እውነት ነው። በእርሱ ከታመንን በእጆቹ መዳፍ ውስጥ ነን፤ ከዚያ የሚያወጣን ማንም የለም። እግዚአብሔር በዚህች ምድርና በዚህ ዕድሜ ብቻ ቅዱሳንን ሳይሰናከሉ የሚጠብቅ ብቻ አይደለም። ከዚህም ባሻገር በክብሩ ፊት በደስታ ነውር የሌላቸው አድርጎ የሚያቆም አምላክም ነው። ክብሩ በታላቅ ግርማ ሊፈርድ በዙፋኑ የሚቀመጥበት ነው። ቅዱሳኑ በዚያ ክብር ፊት ያለ ነውር ሆነው በደስታ ይቆማሉ። ደስታ የተሰኘው ቃል ታላቅ ደስታ ወይም ሐሴት ነው።

ይህን ለሚያደርገው ጌታ፥ ‘ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፥ አሜን።’ አሜን።





# ምዕራፍ አራት

# አስተውሎት

በዚህ ክፍል የተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች ተካትተዋል። እነዚህ ሊዘነጉ የማይገባቸው፥ ብዙውን ጊዜ ግን የማይስተዋሉ ነጥቦች ና ቸው። አንዳንዶቹ መስተዋል የተገባቸው ገንቢ ነጥቦች ሲሆኑ ሌሎቹ የተለያዩ የስሕተት ገጽታዎች ናቸው። እነዚህ ነጥቦች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በአገራችንም ለሚታዩት ለተሳሳቱ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎሞችና እነዚህ አተረጓጎሞች በብዛት በሚስተዋሉባቸው ካሪዝማዊ ልምምዶችና ችግሮች መንገድ የጠረጉ፥ በር የከፈቱ፥ ወይም ከተከፈተ በኋላ የገቡ ናቸው። እኒህን ነገሮች ማወቁም ማስተዋሉም ለመጠንቀቅም ሌሎችን ለማስጠንቀቅም ጠቃሚ ይሆናሉ።

## ከስሕተቶች ጀርባ

መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳቱ መንገዶች የሚተረጉሙ በርካታ አገልጋዮች መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የተጻፈው እውነት ይልቅ በቀጥታ መንፈስ ቅዱስ እንደተናገራቸው አድርገው የሚያቀርቡት ማብራሪያ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቃሉም እንዲጻፍ ያደረገና የጸፉትንም የመራ አምላክ ነውና በቃሉ ውስጥ ያለውን እውነት ሊከስትና ሊያብራራ ይችላል። ግን፥ እነዚህ ሰዎች የሚሰጡት ትርጓሜ በግልጽ ከተጻፈው ጋር የሚጋጭ ከሆነ ቆም ብሎ ማስተዋሉ የሚበጅ ነው። መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያልሠራበት ዘመን አልነበረም። አለ ካልን አባባላችን አንጻራዊና መጠናዊ ብቻ ነው፤ ሰው ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ከቶም ሊድንና ደኅንነትን ሊለማመድ አይችልምና። ያለ እርሱ እርዳታም ትልቅ ወይም ትንሽ ፍሬያማ የወንጌል ተግባርን ሊያከናውን አይችልም። ያለእርሱም እርዳታ በመከራና ስደት ውስጥ ጸንቶ ማለፍ አይቻልም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፥ ጨለማው ዘመን ተብሎ በሚታወቀው መካከለኛው ዘመንም እንኳ ውብ ሥራዎች ተሠርተዋል። ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ በተለያዩ ቦታዎች ህያው ዘአካልነትዋን በድርጅትነት፥ መንፈሳዊነትዋንም በዓለማዊነትና በፖለቲካ የለወጠችባቸው ጊዜያት አልጠፉም። አሁንም አለ፤ ወደፊትም ይኖራሉ። ይህንን እየተቃወሙ የተራመዱ፥ ተቃውሞው ነጥሮ በላያቸው ወድቆ የተጨፈለቁም አሉ። ከግለ